| ይዘት | ገጽ |
|---|---|


የብስራት መፅሄት መልዕክት.....................................................46

ድርጅታዊ መግለጫ.............................................................47

የማያባራ ማዕበል.............................................................49

ፅኑ መሠረት...................................................................55

ቃለ-መጠይቅ ከታጋይ መኮነን ተስፋይ........................................56

ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች........................................................69

የተባበረ ክንድ ለማይቀረው ድል..............................................72

ሐቀኛ ሚድያ...................................................................76

ወታደራዊ ዘመቻዎች.........................................................78

ግጥም..........................................................................87



ቴሌፎን...........................00291-153947

ፋክስ...............................00291-153946

ፖስታ ሳጥን ቁጥር...............1653

ዌብ-ሳይት............ www.demhitonline.com

www.tpdm.net

ኢ-ሜይል............. tpdm1993@yahoo.com

# የብስራት መፅሄት መልዕክት

የድርጅታችን ልሳን የሆነችው ብስራት መፅሄት በ1999 ዓ/ም አሃዱ ብላ የመጀመሪያ እትም ከጀመረች እስከ አሁን ድረስ፡ በአገራችንና በህዝባችን ጉዳይ እንዲሁም ህዝባዊ ትግላችንን አስመልክታ የተለያዩ አጀንዳዎችን በማንሳት በ23 እትሞች ለንባብ በቅታለች።

አሁን ደግሞ እንኳን ለ2ኛው የትህዴን ድርጅታዊ ጉባኤና ለአዲሱ አመት 2009 ዓ/ም አደረሰን፤ አደረሳችሁ፡ እያለች ለ24ኛ እትሟ በከፍተኛና በጠነከረ መልኩ የተለያዩ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመያዝ ቀረባለች።

ብስራት መፅሄት በአሁኑ እትሟ በሃገራችን እያጋጠመ የቆየውንና እስከ አሁንም ያሉትን ህዝባዊ ተቃውሞዎች በአገራችን እየተካሄዱ ከመጡት ምርጫዎች ጋር ተያይዞ ወዴት አቅጣጫ እያመራ እንዳለ **"የማያባራ ማዕበል"** በሚል አጭር ርዕስ ዳስሳዋለች።

የድርጅታችን አመሰራረት እንዲሁም የትግሉን አስፈላጊነትና ወቅታዊነት አስመልክታ ደግሞ **"ፅኑ መሠረት"** በሚል አጭር አርእስት ማብራሪያ ከሰጠች በኋላ፤ የትህዴን ከፍተኛ አመራር ከሆነው ታጋይ መኮነን ተስፋይ ጋር ያካሄደችው ቃለ መጠይቅ ለንባብ ታቀርባለች።

ትህዴን ድርጅት ከተመሰረተ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴው ምን እንደሚመስል፡ **"ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች"** በሚል አርእስት እንዲሁም፡ **"ሐቀኛ ሚድያ"** በሚል አጭር ርዕስ ደሰሳ የሚድያ ክፍል ስራዎች የአሁኑ የብስራት መፅሄት እትሟ አንዱ ይዘት ሆኗል።

በመጨረሻ ደግሞ ትህዴን በኢህአዴግ ስርዓት ወታደሮች ላይ የወሰዳቸው ሰፋፊ ወታደራዊ እርምጃዎች በመዳሰስ የአሁኑ እትሟ **"የስኬት ጎዳና"** በሚል ግጥም የንባብዋን ማሳረጊያ ታደርጋለች።

በዚህ አጋጣሚ ብስራት መፅሄት ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን እየተቀበልነው ያለን አዲስ አመት 2009 ዓ/ም ብሩህ ዘመን እንዲሆንለት መልካም ምኞቷን በመግለፅ፡ እንኳን ለታሪካዊው 2ኛው የትህዴን ድርጅታዊ ጉባኤ አደረሰን አደረሳችሁ ትላለች፡ መልካም ንባብ፦

## ድርጅታዊ መግለጫ

የኢትዮጵያ ህዝብ ከትውልድ እስከ ትውልድ፡ ከጥንት ዘመናት ጀምሮ ከሩቅና ከቅርብ የገዥዎች ጦር የተወረወረበት፣ ለማንበርከክና ነፃነቱን ለመንጠቅ፡ የባዕዳን ወራሪዎች አፈሙዝ የተወደረበት ህዝብ ቢሆንም እንኳ፡ አልምበረከክም ነፃነቴን አሳልፌ አልሰጥም ባይነቱ ግን ቃላት ብቻ ሆኖ አልቀረም። የባዕዳን ወራሪዎችን መድፍና መትረየስ በጦርና በጋሻ መክቶ ነፃነቱን ሊጎናፀፍና በቅኝ ገዥዎች ስር ለሚኖሩ ጥቁር ህዝቦች የነፃነትና የፅናት ተምሳሌት ለመሆን የበቃ ታጋይ ህዝብ ነው።

ለባእዳውያን ወራሪዎች የማይደፈር እምባ መሆኑን በተግባራዊ ቋንቋ የነገረ ህዝብ ሳለ፡ መጥፎ አጋጣሚ ሆኖ ከዘመነ መሳፍንት አንስቶ ከማህፀኑ የወጡ በየወቅቱ የስልጣን ኃይል የተቆናጠጡ ነገስታት፡ ነፃነቱንና የአገሩን ክብር በደሙና በአጥንቱ ያረጋገጠውን ህዝብ ለማንበርከክ ጭቆናዊ አስተዳደር ለማስፋፋት ተፈትነዋል። ይሁን እንጂ ይህ ህዝብ ሃይሉ በአንድነቱ፣ በፅናቱ፣ በኢትዮጵያዊ ማንነቱ ክብር፡ የተመረኮዘ ህዝብ ስለሆነ በጠመንጃ ሃይል ተማምነው እንገዛሃለን ያሉትን መሳፍንትና ፋሽስት በክቡር ደሙንና መስዋዕትነቱ ጠራርጎ ጥጋቸውን አስይዟቸዋል።

ሌሎችን ተጋድሎዎች ትተን ፋሽስታዊ ስርዓት አስፋፍቶ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እንደፍላጎቱ መደለቅ የጀመረውን የደርግን ስርዓት ገና እያለ ለመደምሰስ በተካሄደ መራራ ትግል በገንዘብ የማይተመን ከባድ ዋጋ ከፍሏል። በዚህ የትግል ጉዞ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች በላይ ከባድ መስዋዕትነት የከፈለ ህዝብ ደግሞ የትግራይ ህዝብ ነው። የትግራይ ህዝብ ተወዳዳሪ የሌለው መስዋዕትነት በመክፈሉ በደርግ ላይ ያነጣጠረው የትጥቅ ትግል በድል ተጠናቋል።

ይህ ሁሉ ደም የፈሰሰ፣ ይህ ሁሉ ወጣት የህዝብ ልጆች እምቡጥ ህይወት የተከፈለ፣ የህዝብ ንብረት የወደመው ግን እየታዘብነው እንዳለነው የህዝብን የመስዋዕት ፍሬ ከንቱ የሚያደርግ፡ በደርግ ምትክ ሌላ ዓመፀኛ ለመተካት አልነበረም። ይሁን እንጂ ይህንን በኢትዮጵያ ህዝቦች መስዋዕትና ስንክልና የመጣ ስልጣን በወያኔ ኢህአዴግ መሪዎች በሃይል ተነጥቆ የጥቂቶች ማላገጫ ነው የሆነው። አላማውን አምኖ በትግሉ ሁለመናውን የገበረ ህዝብም ሁሉ ነገሩን ተክዷል።

እነሆ የህዝብ መስዋዕትና ስንክልና ውጤት ሲኮማተር፣ ወንድም እህቶቻችን የወደቁበት መስመር አቅጣጫውን ሲስት፣ ዋጋ ከፍለን ያመጣነው ስልጣን ተመልሶ የህዝብ መጨፍጨፊያ ሲሆን፣ በአጠቃላይ የትግሉ አላማዎች ሲካዱና በላያቸው ላይ ፀረ ዴሞክራሲ ተግባሮች ሲያንሰራሩ ታዝበን ልባችን ስለቆሰለ፣ የሰማእቶቻችን አጥንት እንቅልፍ ሊነሳን ሲጀምር ገና ከጅምሩ የጨነገፈ የህዝባችንን ጥያቄ አንግበን ከግቡ ለማድረስ፡ የካቲት 19 ቀን 1993 ዓ.ም የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) በሚል ተደራጅተን ጠመንጃ አንስተን በረሃ ልንወጣ ተገደናል።

ክቡራትና ክቡራን፦ ይህንን እሳት የሚተፋ የትግል መድረክ ደፍረን ስንገባው የሚጠይቀውን ከባድ ዋጋ ወይም ደግሞ የመስዋእትና ስንክልና ትርጉም ምን እንደሆነ ጠፍቶን አይደለም። ይሁን እንጂ ለህዝባችንና ለሃገራችን ደም እያስለቀሰ ያለው ስርዓት የሚወገድበት አማራጭ ይሄ ብቻ ስለሆነ ነው።

ስለዚህ ይህ ሳንወድ ተገደን የገባነው በህወሃት ኢህአዴግ ላይ ያነጣጠረ የትጥቅ ትግል ይዞት የተነሳ የመታገያ አላማና ፕሮግራም፡ ወቅታዊና ፍትሐዊ፣ የህዝብን ጥያቄና ፍላጎት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ብዙ ተከታዮችን አግኝቶ እስካሁን እያጋጠሙት ለመጡ የትግል መሰናክሎች ተቋቁሞ ረጅም ርቀት ሊጓዝና በአገራችን ተፈላጊና ወሳኝ ትግል ለመሆን በቅቷል።

ድርጅታችን እስካሁን ድረስ ባካሄደው ጉዞ እንዳልነበር ለማድረግ ከእለተ ልደቱ አንስቶ በጠላታችን ማለቂያ የሌላቸው የመርዝ ፈተናዎች ተደርገዋል። ይሁን እንጂ በአገራችንና በህዝባችን ታሪክ ተንበርካኪነት ነውር ስለሆነ፣ ይህ ትግል መሠረታዊ የህዝብ ጥያቄን ስለያዘ፣ በፅኑዎችና የማይወላውሉ ታጋዮች ሁሉንም እያመከነ አሁን ካለንበት መድረክ ላይ ደርሷል።

ክቡራትና ክቡራን፡- ድርጅታችን በእነዚህ ባሳለፍናቸው 15 ዓመታት አወንታዊና አሉታዊ ጎኖቹን በመገምገም ወደ ተሻለ ደረጃ ለመሸጋገር ያተኮሩ አራት ታላላቅ መድረኮች አስተናግዷል። ሦስት ኮንፈረንስና አንድ ታሪካዊ ድርጅታዊ ጉባኤ፡ በእነዚህ መድረኮች በኩል ለሚያጋጥሙት እንቅፋቶች እያስወገደ ስለመጣ ደግሞ እነሆ አምስተኛ መድረክ 2ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ለማካሄድ በቅቷል።

ስለዚህ ሁላችሁም የትግላችን ወዳጆች፣ ደጋፊና ተከታዮች፡ ድርጅታችን ትህዴን እስከ ዛሬ ከፊቱ የገጠሙትን ማዕበልና ውርጅብኝ ተሻግሮ አሁን ወደ አለንበት 2ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ለመድረስ በተደረገ እርብርብ ድጋፋችሁ ስላልተለየን እንኳን አደረሳችሁ አደረሰን ለማለት እንወዳለን።

ይሄ መድረክ ዝም ብሎ የመጣ አይደለም። ትግላችንን ለመቅጨት እንዳልነበረ ለማድረግ በጠላታችን ከተሴሩ የጥፋት መርዞች ጋር ገጥመን ከባድ ዋጋ ከፍለንበታል። ምክንያቱም ሱሪ አጥልቀን የጀመርነውን ትግል ለጥፋት ኃይሎች አሳልፎ መስጠት፡ ታሪክህን ከማበላሸት አልፎ የአገርንና የህዝብን ታሪክ ማበላሸት ስለሆነ ትግላችን አሁንም ቀጣይ ነው።

ትግል እንደስሙ ትግል ስለሆነ ከእንግዲህም መሰናክል አያጋጥመንም አንልም። ግን ደግሞ ያለንን የትግል ተሞክሮ በ2ኛ ድርጅታዊ ጉባኤያችን እንዲጠናከር በማድረግ በእኛ ላይ ለሚታለም የጥፋት ሴራ እያመከንን የትግል ድላችንን ለማቀላጠፍ ጠንክረን እንረባረባለን።

ስለዚህ ሁላችሁም የትግላችን ወዳጆችና ደጋፊዎች፡ እንዲሁም ኣባሎቻችን የኢትዮጵያ ህዝብ እየተመኘው ያለውን የስርዓት ለውጥ በአጭር ጊዜ ገሃድ ለማድረግ እያካሄድነው ባለነው የትጥቅ ትግል ድርሻችሁን እንድታበረክቱና ድጋፋችሁ እንዳይለየን፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ጀምረኸው ያለኸው በስርዓቱ ላይ ያነጣጠረ ህዝባዊ ተቃውሞ ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ አጠናክረህ እንድትቀጥልበት ጥሪያችንን እናቀርባለን። ትህዴን ዛሬም እንደቀደሙ የወያኔ ኢህአዴግ ስርዓትን ዕድሜ ለማሳጠር በአንዲትና ጥምርት ኢትዮጵያ ከሚያምኑ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ተባብሮና ተቀራርቦ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ደጋግሞ ያረጋግጣል።

የተከበራችው የትህዴን ታጋዮች፡ የህዝባችሁ ስቃይ ተሰምቷችሁ፣ የአገራችን ውርደት ውርደታችን ነው ብላችሁ፣ ህዝባችንንና አገራችንን ፀረ ዴሞክራሲ ከታጠቀው የድህነት ዋርድያ የሆነ በቋሙ ከበሰበሰ ስርዓት ነፃ ለማውጣት የጀመራችሁትን ተጋድሎ ከግቡ ለማድረስ ከማንኛውም ጊዜ በላይ 2ኛ ድርጅታዊ ጉባኤያችን ለሚወስናቸው ውሳኔዎች ተግባራዊ ለማድረግ ጠንክራችሁ ልትረባረቡና ቃላችሁን ልታድሱ፣ የሰማእቶቻችሁን አላማ ከግቡ ለማድረስ እንድትረባረቡ ድርጅታችሁ ጥሪውን ያቀርባል።

በመጨረሻም ይህ እየተቀበልነው ያለነው የ2009 አዲስ ዓመት መልካም ዘመን ይሆንልን ዘንድ መልካም ምኞታችንን እየገለፅን፡ ድርጅታችን ትህዴን የህወሃት-ኢህአዴግ ስርዓትን ለማስወገድ እየተካሄደ ላለው ትግል ማንኛውንም ዓይነት አማራጭ ይወስዳል። ድልና ድምቀት ለ2ኛ ድርጅታዊ ጉባእያችን! ክብርና ሞገስ ስለ ህዝብና ስለ ሃገር ለወደቁ ሰማዕቶቻችን ይድረሳቸው።

ድል ለጭቁኖች!!
ነሃሴ 2008 ዓ/ም

**የማያባራ ማዕበል!!**

የትግራይ ህዝብ በገዢ መደቦች በላዩ ላይ ሲደርስበት ከነበረው መደባዊና ብሄራዊ ጭቆና ተላቅቆ ወደ አዲስ የዴሞክራሲያዊ መድረክ እንዲሸጋገር፡ ተስፋዎችን ሰንቆ በዘውዳዊው የኃይለስላሴ ስርዓት ላይ ሲካሄድ የነበረው ህዝባዊ አመፅና ያልተደራጀ ትግል የበኩሉን በማበርከት፡ በዩንቨርስቲ ተማሪዎች ሲካሄድ የነበረው ለስርዓቱ አንቀጥቅጦት በነበረው አመፅ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ከኃይለስላሴ ስርዓት ውድቀት በኋላም የህዝቡን ዓመፅ ተጠቅሞ የስልጣን ወንበሩን የተቆናጠጠው ደርግ የአፈና መረቡን ሊዘረጋና የኔ ተገዢ ሁኑ የሚል አዋጅ ሲያውጅ ጊዜ ስላልወሰደ፡ የትግራይ ህዝብ በድብቅ ሲካሄድ የቆየውን ትግል በከፍተኛ መልኩ በመቀጠል የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ/ም ጠመንጃ አንስቶ ደርግን ለመፋለም በረሃ ወጣ።

ብዙ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ ደግሞ ለ17 አመታት ያህል የተካሄደው መራራ የትጥቅ ትግል ዓለምን ጉድ ያሰኘ ታሪኮች ፈፅሟል። ተራራና ተዳፋቱ እየተባለ ሲተረትበት የነበረው የደርግን ስርዓት ድባቅ መቶታል። የትግራይ ህዝብ ይህንን ሲያደርግ ግን ከባድ ዋጋ ከፍሎ ነው። ለዚህ ከባድ ዋጋ ሲከፍል ደግሞ ገሃድ እንዲሆንለት የሚመኘው ራኢና አላማ ነበረው።

አምባገነንነትና ልዩነት አብቅቶ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በመገንባት በሰላምና በፍቅር፡ ከሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር አብሮ ለመኖርና የዴሞክራሲን ጣዕም ለማጣጣም የሚል ተስፋና ምኞት ነበረው። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ በትግሉ ጎራ ተሰልፎ ሊገፋተር ይችላል ተብሎ የማይገመተውንና እስከ አፍንጫው ድረስ ከታጠቀው ደርግ ጋር ገጥሞ በትግሉ ጠራርጎ አስወግዶታል። ይሁን እንጂ ተስፋዎች ግን ወዲያውኑ ጊዜ ሳይሰጥ ጨልሞበታል።

የትግራይ ህዝብ የታገለላቸው አላማዎች ተረስተው የሰማእታት ደም ሳይደርቅና ሰውነታቸውና ሥጋቸው ሳይለያይ አደራቸው ከተካደ በኋላ፤ በአዲሱ መቃብራቸው ላይ ፀረ ዴሞክራሲ ተግባራት ተመልሶ ለማንሰራራት ሲጀምር ህዝባችን ደግሞ ቸኩሎ ወደ እርምጃ አልገባም። ከግንቦት 20 1983 ዓ/ም ድል ማግስት ጀምሮ ለ10 አመታት ያህል በትዕግስትና በአርቆ አሳቢነት ህወሓት ሊያሻሽል ይችላል በሚል ተስፋ ጠበቀው። ከዚህ ጎንለጎን ደግሞ ህዝብ በየተመቸው መንገድ አንዳንዱ በድብቅ በስርዓቱ ጉያ ስር በመሆን ሲንቀሳቀስ፣ ሌላው በስደት መልክ፣ በሸፍትነት መልክ፣ ሌላው ደግሞ ከተቃዋሚ የኢትዮጵያ ድርጅቶች ጋር በመሆን ተቃውሞውን ሲገልፅ ቆይቷል።

ይሁን እንጂ ህወሓት የአፈናና ጸረ ዴሞክራሲ መረቡን ሊያስፋፋ እንጂ ሊያስተካክል አልቻለም። ኢ.ህአዴግ ኢትይጵያን ሊጠቅማት የሚችል ፌደራላዊ ስርዓት ነው የምከተለው፣ በመድብለ ፓርቲ የታነፀ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ነው የማምነው፣ በማለት በየአምስት አመቱ ምርጫ ያካሂዳል። በነዚህ በየጊዜው ሲካሄዱ በነበሩት ምርጫዎች ደግሞ በርከት ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ይሳተፉ እንጂ ድል አድርገው ግን ታይተው አያውቁም።

ምክንያቱም የሚካሄደው ምርጫ ፍትሃዊነትና ቅንነት የጎደለው ስለሆነ። ኢ.ህአዴግ ራሱ አስመራጭ፣ ታዛቢ፣ ራሱ ደግሞ መራጭ ሆኖ ስለሚያካሂደው የምርጫ ሳጥኑ በእጁ ቁጥጥር ነው። በፈለገው ሰዓት እንደፈለገው ነው የሚያደርገው። ህዝብ ነፃ ሆኖ መምረጥ አይችልም ነፃነቱን ተጠቅሞ የመሰለውን እንዳይመርጥ የተለያዩ አፋኝ ተፅእኖዎች ስለሚወርድበት ነፃ ሆኖ ሊመርጥ ይሁን ሊመረጥ አይችልም፡ መብት የሚባል የለም። ለዚህ ሁሉም መሰናክሎችን አልፈው በድምፅ ያሸነፉት የተቃዋሚ ድርጅቶችን ደግሞ በማጥላላት አስሮ ሲቀጠቅጣቸው ለአንዳንዶቹም አሸባሪ በሚል ስም የነሱን ምስል በማይገልፅ ሲፈርጃቸው እያየን መጥተናል።

ኢ.ህአዴግ ወደ ስልጣን ከወጣ እስከ አሁን ድረስ አምስት ምርጫዎች አካሂዷል። በ1987 ዓ/ም የመጀመሪያ ምርጫ፣ በ1992 ዓ/ም ሁለተኛው ዙር ምርጫ፣ በ1997 ዓ/ም ሶስተኛ ዙር ምርጫ፣ በ2002 ዓ/ም ደግሞ አራተኛ ዙር ምርጫ ተካሄደዋል። ከአምስት አመት በኋላም በ2007 ዓ/ም አምስተኛው ዙር ምርጫ ደረሰ።

እነዚህ ምርጫዎች ደግሞ የየራሳቸው እንከኖች ትተው ነው ያለፉት። ለአብነት እንኳ ብንጠቅስ፡- 3ኛ ዙር ምርጫ ስናይ በፊት ከነበሩት ሁለት ምርጫዎች ትንሽ የዴሞክራሲ ጭላንጭል የታየበት ስለነበረ ህዝብ በኢ.ህአዴግ ላይ ቀይ ካርድ የደቀነበት ምርጫ ነው የነበረው።

የምርጫው ውጤትም ምን እንደሚመስል ገና ከጅምሩ የተረዳው የስርአቱ ጠቅላይ ሚንስትር የነበረው መለስ ዜናዊ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ/ም በቴሌቪዥን መስኮት ቀርቦ፡ ከዛሬ ቀን ጀምሮ ለ30 ቀናት ያህል ምንም አይነት ህዝባዊ ስብሰባ ማድረግ አይፈቀድም። ፌደራል ፖሊስ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለጠቅላይ ሚንስትሩ ሆኗል። ሲል የስርዓቱን ጸረ ዴሞክራሲያዊ ባህሪው በጉልህ ያሳየበትን መምሪያ አወረደ።

በሰኔ ወር 1997 ዓ/ም ኢ.ህአዴግ በምርጫው በከፍተኛ ድምፅ እንዳሸነፈ የምርጫ ቦርዱ በመግለፁና ተቃዋሚዎች ምርጫው መደገም አለባት ያሏቸውን ቦታዎች አብዛኛዎቹ በመከልከላቸው የተነሳ በየከተማው የህዝቡ ቁጣ ተቀጣጠለ። በጊዜው ደግሞ ኢ.ህአዴግ ብዙዎችን ገድሎ ብዙዎች ካቆሰለ በኋላ ለመረዳዳት አወንታዊ ወይም በጎ አመልካከት ስላሳየ በመጠኑም ቢሆን መረጋጋት አሳየ። ይሁን እንጂ ብዙ ሳይቆይ በቀጣዩ አመት ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ/ም ነገሩ ወደ ከፋ ግርግር በማምራት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚንስትሩ የሆነው የፌደራል ፖሊስ ሃይል መንግስት ባመነበት ብቻ የ193 ዜጎችን ህይወት ቀጠፈ።

ከተወዳደሩት የተቃዋሚ ድርጅቶች በተለይ ብዙዎች የስርአቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት የተወዳደሩበት አዲስ አበባ ከተማ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ አሸንፈው ነበር። ይሁን እንጂ ኢ.ህአዴግ ካጋጠመው ሽንፈት ተንተርሶ በጠመንጃ ሃይል ሲያምፅ ታይቷል። በውጤቱም ከ200 በላይ የሚሆኑ ንፁሃን ዜጎች በአውራ መንገድ በጥይት ተገድለዋል። የድርጅቶች አመራሮች በጅምላ ወደ እስር ቤት ታጉሮው ከባድ በደል ደርሶባቸዋል። በኋላም

በደረሰባቸው ግፍ በመሰናበድ ወደ ውጭ ሃገሮች ተበታተኑ። ስርዓቱ ደግሞ የደረሰበትን ሽንፈት በእንደዚህ አይነት እርምጃ አድበስብሶት አለፈ።

የ2002 ዓ/ም ምርጫ ቢሆንም ወያኔ ከ1997 ዓ/ም ትልቅ ትምህርት አግኝቶ ስለቆየ፡ የምርጫውን አፈፃፀም አስቀድሞ ነው ጨርሶት የቆየው። ገና ምርጫው ሳይጨረስ የመራጮች ካርድ ሳይቆጠር 99.6% አሸነፍኩኝ ብሎ አወጀ። የምርጫውን አፈፃፀም በሚመለከት ግን ለመናገር  የሚያሳፍር ነው የነበረው።

የ2007 ዓ/ም ምርጫ ስናይም ከ2002 ዓ/ም በማይለይ መልኩ በማደናገርና በማጭበርበር ሰለተካሄደ አስቀድመውም ጨርሰውት ስለቆዩ፡ ኢህአዴግ መቶ ከመቶ አሸነነፍኩኝ ብሎ ጨርሶታል። ተቃዋሚዎች እሪ ቢሉም የሚሰማቸው አላገኙም። ምክንያቱም የህግ አስፈፃሚዎችም ራሳቸው ከፍተኛ የስርአቱ ባለስልጣናት ስለሆኑ። “ጅብ ፈርተው ዛፍ ላይ ቢሰቀሉ ነብር አገኛቸው” እንደሚባለው  ነው የገጠማቸው።

በድምሩም እነዚህ እስከ አሁን ድረስ ተካሄዱ የተባለላቸው አምስት ዙር ምርጫዎች ለይስሙላ ተካሄዱ እንጂ አላማቸው ለለውጥ ታስቦ አይደለም። ለይስሙላ በፖለቲካ ውድድር የሚያምን ነው ተብሎ እንዲነገርለት ብቻ የታሰበ የማደናገሪያ አጀንዳዎችን ያዘሉ ነው የነበሩት። ስለዚህ የኢህአዴግ ስርአት ወደ ስልጣን ከወጣ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በፖለቲካዊ ትግል አድርገህ ከስልጣኑ ለማስወገድ የተካሄደ ትግል ውጤታማ አልነበረም።

ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ኢህአዴግ የሚባል ስርዓት በፖለቲካዊ ትግል ስልጣኑን ሊያስረክብ የሚችል ስርአት እንዳልሆነ ሙሉ በሙሉ አረጋግጧል። የፖለቲካ ድርጅቶችም ቢሆኑ ትግሉን ማቋረጥ ስለተሳናቸው እንጂ ተስፋ በሌለው ነገር የጊዜ መስዋእትነት እየከፈሉ መሆናቸውን ያውቃሉ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ከ5ኛው ዙር ሃገራዊና ክልላዊ የሃገራችን ምርጫ በሁዋላ ሲያጋጥሙ የመጡትን በህዝቡ የተነሱ ተቃውሞዎች በቁጥራቸው በርከት ያሉ ቢሆኑም እንኳ ዋና ዋናዎቹን በወሳኝ መልኩ ነካ ነካ እናደርጋቸዋለን መልካም ንባብ፡-

በጋምቤላ ክልል ሙርሌ በተባሉት የታጠቁ የደቡብ ሱዳን ሃይሎች በተከሰተው ዘረፋ ከ225 በላይ የጋምቤላ ክልል ተወላጆች ሲገደሉ፣ 225 የሚሆኑ ህፃናት ደግሞ ታፍነው ሲወሰዱ፣ ከ2000 በላይ የሚሆኑት የጋምቤላ ህዝብ ከብቶች ደግሞ በነዚህ ከደቡብ ሱዳን በመጡት የታጠቁ ሃይሎች ተወስደዋል። ይህ ደግሞ ስርዓቱ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ አስተማማኝ ሊያደርገው ባለመቻሉ የተከሰተ ችግር ነው። ከክልሉ ሳንወጣም በአኝዋክና ሙርሌ በተነሳው ቀጣይነት ያለው ግጭት በሁለቱም መካከል በአስራዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል።

የኢህአዴግ ስርዓት አዲስ አበባ ከተማን ከኦሮምያ ክልል አገናኛቸዋለው በማለት ያነሳው ሃሳብ የህዝቡን ጥቅም መሰረት ያላደረገ ማስተር ፕላን በመሆኑ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጥሞታል። ይህ ከህዳር ወር እስከ ግንቦት ብሎም እስከ አሁን ድረስ በመላ አካባቢዎች እየተቀጣጠለ ያለውን የህዝብ ተቃውሞ ለማስቆም በወሰደው የሃይል እርምጃ ደግሞ ከ400 በላይ ወገኖች ሲገደሉ፣ ከ10 ሺ በላይ የሚሆኑት ደግሞ ታስረዋል። ይህ ፍፃሜ ደግሞ ስርአቱ የህዝቡን ጥቅም ሳይጠብቅና ሳያረጋግጥ በመሄድ ላይ እንዳለ የሚያመላክት ነው።

በደቡብ ህዝቦች ውስጥ የሚኖር የቁጫ ብሄረሰብ እኛ ጋሞ አይደለንም። ወላይታም አይደለንም ቁጫ ነው ማንነታችን ህጋዊ እውቅና ሊሰጠን ይገባል የሚል ጥያቄ አንስቶ ነበር። ስርአቱ ደግሞ ህጋዊ መልስ ከመስጠት ፈንታ አነሳሾች ናቸው ያላቸውን ሰዎች ስላሰራቸው ጥያቄያቸው እስከ አሁን ድረስ ዘላቂ መፍትሄ ሊያገኙ ስላልቻሉ በከፍተኛ ግጭት ገብተው ይገኛሉ። የተለያዩ አካላት ጉዳዩ በሰከነ መንፈስ ታይቶ ተገቢው መልስና መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል ቢሉም እንኳ ስርአቱ ግን እስከ አሁን ድረስ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎት ይገኛል።

በሌሎች በርካታ ዞኖችና ወረዳዎች የሚገኙ የደቡብ ክልል ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳችን በራሳችን እናስተዳድራለን የሚል ጥያቄ ተነስቷል። ሰገን አካባቢ በተባለው ዙሪያ ባለው ዞን ውስጥ ያሉት ጎሳዎች አንዱ የሆነው የኮንሶ ብሄረሰብ ራሱ-በራሱ የሚተዳደርበት የዞን አስተዳደር እንዲኖረው በማስመልከት ያነሳው ጥያቄ አመታትን አስቆጥሮ ይገኛል። ይሁን እንጂ ይህም በስርአቱ ተቀባይነት ስላላገኘ ትገቢውን ምላሽ ሳይሰጠው ተዳፍኖ በመሄድ ላይ ያለ ሌላው አደጋ ነው።

አማራ ክልልም ተቃውሞ ያልተለያት ክልል ሆና እናገኛታለን። ለምሳሌ በክልሉ ሲኖሩ የነበሩትን 142 የሚሆኑ ጣብያዎች የቅማንት ብሄረሰብ ራሳቸው በራሳቸው ሊያስተዳድሩ ሲጠይቁት የቆዩትን የማንነት ጥያቄ ተከትሎ። ለ42 ብቻ መልስ ሰለተሰጣቸው አንድ አይነት ባህልና ልምድ ያላቸው ብሄረሰቦች እንደዚህ አይነት ልዩነት ያለው አካሄድ መከተል ፍትሃዊ አይደለም በማለት ከአካባቢው አስተዳደር ጀምሮ እስከ የክልሉ ፌደረሽን ምክር ቤት ህገ-መንግስታዊ መብታችን ይከበርልን ብለው ጥያቄያቸው ያቀረቡ እንኳ ቢሆኑም ሰሚ አካል አላገኙም። የዚህ ውጤትም ህዳር 30 ቀን 2008 ዓ/ም በአማራና በቅማንት መካከል ግጭት ስለተነሳ በስርአቱ በርካታ ዜጎች ሲገደሉ ብዙዎችም ታስረዋል።

በተነሳው ግጭት ላይ 33 ንፁኃን ዜጎች የተገደሉ ሲሆን፣ በአስራዎች የሚቆጠሩ ወገኖችም ቆስለዋል። ቁጥራቸው በውል ያልታወቁት ደግሞ በጊዜው የታሰሩ ሲሆን፣ ከአራት ወረዳዎች ብቻ 150 ሚልዮን ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል። ይህንንም ተከትሎ ታህሳስ 9 ቀን 2008 ዓ/ም የብአዴን ባለ ስልጣናት ለሁለቱም ህዝቦች ስብሰባ ያደረጉላቸው ሲሆን፣ የቅማንት ብሄረሰብ ተወላጆች "እኛ ማንነታችን ይታወቅልን ራሳችን በራሳችን እናስተዳድራለን ስላልን ብቻ ብአዴን በላያችን ላይ ጥቃት እንዲፈፀም አድርጓል።" ካሉ በኋላ፣ "የቅማንት የማንነት ጥያቄ መልሰነዋል የምትሉት የቅማንትን ብሄረሰብ የሚበታትን ነው። ማለት ከ142 የቅማንት ብሄረሰብ ጣብያዎች 42 ናቸው የተመለሰላቸው። ይህ ደግሞ ልዩነት መፍጠር ነው። ስለምንድነው የማይመለስልን ቅማንት እንደ ቅማንት የየራሱ የሚበታትን ቅኑ ያልሆነ አስተዳደራዊ ተግባር ነው።" ሲሉ ተቃውሟቸውን ገልፀዋል።

ብዙ የሰው ህይወት ከጠፋና ብዙዎች ከታሰሩ በኋላ የስርዓቱ ባለ ስልጣናት፣ "ህገመንግስታችን ያልመለሰው የማንነት ጥያቄ የለም።" ሲሉ እንዳልነበሩ በአሁኑ ጊዜ ጥያቄያችሁን ተቀብለነዋል። በዚህ መሰረትም አብዛኛው ህዝብ ውሳኔውን ካመነለት በዛ እንሄዳለን በሚል ቋሚ ያልሆነ አቋም በመስጠት እስከ አሁን ድረስ ሳይፈታ ውስጥ ለውስጥ እየቀጠለ ይገኛል። እንዲሁም በትግራይና በአማራ ክልል መካከል የማንነት ጥያቄ ተከትሎ የተነሳው ግጭት ዘላቂ መፍትሄ ስላልተደረገለት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተቀጣጥሎ በመቀጠል ላይ ስለሚገኝ ዜጎቻችን በተዘዋዋሪ ይሁን በቀጥታ እየተገደሉና እየታሰሩ ይገኛሉ።

በትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ወልቃይት ወረዳና አከባቢዋ የሚኖሩ የወልቃይት ተወላጆች በህወሓት-ኢህአዴግ ስር ሆነው ከሚተዳደሩ ጀምሮ ሲያነሱት ከቆዩት በርከት ያሉት ጥያቄዎች ትኩረት አግኝተው በክልሉ አስተዳደሮች ይሁን በዞኑ ተገቢ ምላሽ ያልተሰጣቸው ህዝባዊ ጉዳዮች፡ “በመሬታችን ተጠቃሚ መሆን አልቻልንም፣ መልካም አስተዳደር የሚባል የለም፣ የገዢው ስርአት አጀንዳዎች እንድንሰማ እንጂ ጉዳያችን ሰሚ አካል አላገኘንም፣ ከአካባቢያችን ያልወጡ ሰዎች ናቸው እያስተዳደሩን ያሉ፣ ለምንድነው ራሳችን በራሳችን የማስተዳደር ህገመንግስታዊ መብታችን የማይከበርልን” የሚሉና ሌሎችም ሲሆኑ እስካሁን ትኩረት የሚሰጠው መንግስታዊ አካል ባለማግኘታቸው የህብረተሰቡ ተወካይ የሆኑ ሽማግሌዎች በጎንደር አካባቢ ተሰብስበው መሰረታዊ መፍትሄ ያመጣል የሚሉትን ውይይት እስከማካሄድ ደርሰዋል።




የዚህ ውጤትም የወልቃይት ህዝብ አማራ ነን የሚል የማንነት ጥያቄ አንስቶ ተቃውሞ አካሂዷል። ስርአቱ ደግሞ ይህንን ጥያቄ ያነሱትን 34 ሰዎች ያለምንም ርህራሄ ገደሏቸዋል። ከ93 በላይ የሚሆኑ ደግሞ በየጊዜው ታፍነው ስለተወሰዱ እስከ አሁን ድረስ አድራሻቸው አይታወቅም።

በዚህም የማንነት ጥያቄ ምክንያትም በርከት ያሉ ዜጎች የተለያየ ግፍ ደርሶባቸዋል፡ 12 የሚሆኑ ነዋሪዎች ደግሞ መኖሪያ ቤታቸውና የእርሻ መሬታቸውን ሲቀሙ፡ 173 ወገኖች ደግሞ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል።

የወልቃይት ህዝብ ያነሳቸው የማንነት ጥያቄ መሰረት ያደረገ ህዝባዊ ተቃውሞ በዚህ አላበቃም። በቅርብ ጊዜም በጎንደር ከተማ በህዝቡና በወያኔ ኢህአዴግ ስርአት ጋሻ ጃግሬዎቹ መካከል ከፍተኛ ተቃውሞ ተፈጥረዋል። በዚህ ምክንያት ደግሞ ህፃናትና ወጣቶች የሚገኙባቸው ከ15 በላይ ሰላማዊ ህዝብ የሞተ ሲሆን ቡዙ ደግሞ ሲቆስሉ። ከአስር በላይ የፌደራል ፖሊስ አባላትም በግጭቱ ሞተዋል። ግጭቱ በወልቃይት ህዝብ የማንነት ጥያቄ የተነሳ ሲሆን ስርአቱ የህዝቡን ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት ፈንታ ጥያቄውን ለመጨፍለቅ የኮሚቴ አመራሮች የሆኑት ሰዎች ለመያዝ ባደረገው ሙከራ የተወሰኑትን ስለያዘና ስላሰረ ተቃውሞውን ሊጋጋል ችሏል።




በጎንደር ህዝብና በወያኔ ኢህአዴግ ስርአት የፀጥታ አባላት መካከል በተፈጠረው ግጭት እየሰፋ ሄዶ በአሁኑ ጊዜ ከስርአቱ ጋር ቅርርብ አላቸው የተባሉት የንግድ ድርጅቶች ጥቃት በማውረድ ሰው አሳፍራ ጎንደር ከተማ በማቋረጥ ላይ በነበረችው አንዲት የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ የተሳፈረውን ህዝብ በማውረድ አውቶቡስዋን በእሳት እንድትጋይ አድርገዋል። ከዚህም ሌላ ከአምስት በላይ የሚሆኑ የፖሊስ መኪናዎች

ተቃጥለዋል። በጎንደር ከተማ የሚገኙ የፖሊስ አባላት ደግሞ ማንኛውም እርምጃ ከመውሰድ በመቆጠብ ከህዝቡ ጋር ሲወግኑ ታይተዋል።

ከዚህ ግርግር ጋር ተያይዞም በቦታው የሚገኙ አንድ አንድ የትግራይ ተወላጆች የሆኑት የንግድ ድርጅቶች የጋዩ ሲሆን የዚህ ጥቃት ተጠያቂ የሚሆነው ደግሞ ራሱ ስርአቱ ነው፡ ምክንያቱም በህዝቦች መካከል ያለመተማመንና መጠቃቃት እንዲፈጠር እያደረገ ያለው ራሱ ስርአቱ በመሆኑ።

በትግራይ ክልል ማእከላዊ ዞን የሚገኝ የእምባ-ስነይቲ ህዝብ ለ20 አመታት ያህል ሲያቀርበው የቆየውን ወረዳችን ይመለስልን የሚለውን ጥያቄ መፍትሄ ሊያገኝ ባለመቻሉ የተነሳ በሺዎች የሚቆጠር ህዝብ ቁጣውን ለመግለፅ በነበለት ከተማ ሚያዝያ 10 ቀን 2008 ዓ/ም ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል።

ላለፉት 25 አመታት ከመሰረተ ልማት አገልግሎት ርቆ የቆየውን ቡዙ ቁጥር ያለው የእምባ ሰነይቲ ህዝብ ቀደም ሲል በእምባሰነይቲ ወረዳ ሲተዳደር የነበረ ሲሆን፡ ያለፍላጎቱ ወደ ወርዒ-ለኽ (ዕዳጋ ዓርቢ ከተማ) ተጨፍልቆ እንዲተዳደር በማድረግ የተለያዩ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ስለሚደርስበት ደጋግሞ ጥያቄውን ለ20 አመታት ያህል ሲያቀርብ የቆየ ቢሆንም እንኳ ተገቢውን ምላሽ ሊያገኝ ባለመቻሉ 60 ኪሎሜትር ያህል በመጓዝ የማህበራዊ አገልግሎት ሊያገኝ ችሏል። በአሁኑ ጊዜ እያነሳው ያለውን ጥያቄ ደግሞ ድካሙን እንዲቀረፍለት በቅርብ እንድንተዳደር የድሮ ወረዳችን ይመለስልን በማለት ከ30,000 ህዝብ በላይ ከፍተኛ ተቃውሞ አካሂደዋል።



የእምባሰነይቲ ህዝብ ብዙ የመሰረተ ልማት ጥያቄ ቢነረውም እንኳ ከሁሉም በላይ እንድትመለስለትና አጥብቆ እየጠየቀላት ያለውን ጉዳይ ደግሞ ወረዳውን የሚመለከት ነው። እምባሰነይቲ ወረዳ ተብሎ እንዲመለስለትና ፍትህ በቅርቡ እንዲያገኝ እንዲሁም ራሱን በራሱ እንዲተዳደር እየፈለገ፡ ጥያቄውን በሰለጠነ መንገድ ደጋግሞ ወደ ስርአቱ አቅርቧል።

ይህንን ሰላማዊ ሰልፍ የተከታተሉት የስርአቱ ካድሬዎችም አንመልስም ምን ታመጣላችሁ በማለት የመለሱለት ሲሆን፡ እንደምክንያት ካቀረቡት ሃሳብ ደግሞ ከ20 አመታት በፊት የነበሩ 81 የትግራይ ወረዳዎች፡ "በጀት ለመቆጠብ" ተብሎ ወደ 35 ወረዳዎች ስለተጨፈለቁ በመላው ትግራይ ተዳፍኖ የቆየውን ተመሳሳይ ጥያቄ ሊነሳ ነው። በመሰረቱ የነበለት ህዝብ ጥያቄ ልማታዊ አይደለም የሚል ነው።

ይሁን እንጂ የህወሓት መሪዎች መሰረታዊና ፍትሃዊ የሆኑ የህዝብ ጥያቄዎች አንመልስም ስላሉ ብቻ ከጫፍ እስከ ጫፍ የሃገራችን ክልሎች ራሳችን በራሳችን እናስተዳድራለን የሚሉ የማንነት ጥያቄዎች፡ እንዲሁም የመሰረተ ልማትና የመብት ጥያቄዎች ሊቆሙ አይችሉም። ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ልክ እንደ እምባሰነይቲ ህዝብ ያለውን የህዝብ ጥያቄ የማይመልስ ድርጅት "ዛሬም ይሁን ነገ ድርጅታችን አይደለም

ቀጣይነት ያለው አቋማችን ነው" በሚል ፅኑ አላማ በማንገብ የጀመረው ተቃውሞ አጠናክሮ እንዲቀጥልበት እልክ የሚያስይዘው ነው።

"የማይነጋ መስሏት ....." እንደሚባለው የህወሓት ድርጅት የበግን ለምድ ለብሶ እያለ ህዝቡን አታልሎ የፈፀመውን የወረዳዎች መጨፍለቅ አሁን ተመልሶ ሊውጠው ፈልጓል። ምናልባት ኢህአዴግ እስከ አሁን ድረስ ሲነሱ የቆዩትን ህዝባዊ ተቃውሞዎች በጠመንጃ ሃይል ሲጨፈልቅ ቆይቷል። ከእንግዲህ ወዲህስ....?

## "ፅኑ መሠረት"

የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ የጦርነት ጥማትና ፍላጎት የለዉም። የዘወትር ህልሙ ሰላም፣ ፍቅርና እድገት ነው። ይህ ህዝብ ከጦርነትና የጦርነት ወሬ ርቆ ሰላም በሰፈነባት አገር አብሮ ለመኖር የሚፈልግ ሰላማዊ ህዝብ ነው። ለደርግ ስርአት የተታገለበት አላማም ለዚህ ያለመ ነበር።

ከደርግ ስርአት ውድቀት በኋላ 10 አመታት በማይሞላ ጊዜ በወያኔ ኢህአዴግ ስርዓት ላይ ያነጣጠረ የትጥቅ ትግል እንዲመሰረት መንስኤ የሆነ ምንድነው ከተባለ ግን...? ራሱ በስልጣን ያለው ስርአት ነው። የህዝብ የመስዋእትነት ፍሬ የሆነ ሰላምና ዴሞክራሲ ዉጦ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ በህዝብ ጫንቃ ላይ መቀለድ ነው የጀመረው፣ እንደ ዉጤቱ ደግሞ ያ ጭቆናና በደል የማይቀበልና የማያፈቅድ ህዝባችን መሳርያውን ታጥቆ መብቴ ማለት ስለጀመረ ለትህዴን መመስረት አንድ በር ከፍቷል።

የልጆቹን የመስዋእት ፍሬ የተካደ ህዝብ ሰላም አግኝቶ ባለማደሩ መብቴ በክንዴ ብሎ ዳግም ወደ በረሃ ወጣ። ከዚህ በመነሳት ደግሞ ቀደም ሲል በረኃ ወጥተው ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተቀላቅለው ሲታገሉ የቆዩ 30 የትግራይ ተወላጆች የትግራይ ህዝብ ወያኔ ኢህአዴግ ለማስወገድ በሚካሄድ ትግል ራሱን ተደራጅቶ ድርሻዉን እንዲያበረክት ስለ ነበረበት ብሄራችን እናደራጃለን የሚል ሃሳብ አንስተው ትህዴንን በመመስረት መንቀሳቀስ ጀመሩ።



እነዚህ የትግል ጓዶች በብሄራቸው ተደራጅተው የትግራይ ህዝብ በማደራጀት የወያኔ ኢህአዴግ ስርአት እንዲያስወግዱ ከነበራቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ወደ ተግባር በመቀየር፣ የትህዴንን ድርጅት ለመመስረት በ28-10-1992 ዓ.ም እስከ 18/06/1993 ዓ.ም በነበሩ ወቅቶች ትህዴን ለመመስረት የምያስፈልጋቸውን አስፈላጊ የሆነ ሁሉ ከተሰራ በኋላ በ19-06-1993 ዓ/ም ድርጅቱ በይፋ ተመሰረተ።

በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተለያዩ የወያኔ ወታደራዊና ስቪላዊ ድርጅቶች በማገልገል ላይ የነበሩ ድብቅ የወያኔ አጀንዳዎችና ፖሊሲዎችን በመቃወም ወደ ኤርትራና ሌሎች አገሮች የመጡ 59 የሚሆኑ ፀረ ወያኔ ኢህአዴግ ስርአት ለመታገል ተነሳሽነት የነበራቸው የትግራይ ተወላጆች ከጥቅምት ሁለት 1993 ዓ.ም ጀምሮ የፕሮፖጋንዳና ቅስቀሳ ስራቸዉን ለመቀላጠፍ ጀምረው ነበር።

በዚህ መካከል ግን ሁለቱም ወገኖች የሁለቱም እንቅስቃሴ ተዋውቀው ስለ ነበሩ ተገናኝተው የመተዋወቅና በጋራ የመስራት ችሎታቸውን እንዲያስተካክሉ ስለ ነበረባቸው ጉንበት 4 ቀን 1993 ዓ/ም የሁለቱም ወገን ጊዚያዊ አመራሮች በሞሎቨር ከጀላይ በተባለ ቦታ ተገናኝተው ንግግር በመካሄድ ስለተስማሙ ሰራዊታቸውን ወደ አንድ በመቀላቀል አዲስ አደረጃጀት በመፍጠር ትግሉን ማቀጣጠል ነው የጀመሩት።

የተከበራችሁ የትህዴን ድርጅት ብስራት መፅሄት አንባቢያን ትህዴን ከአስር አመት የኢ.ህአዴግ ስልጣን ብኋላ በ1993 ዓ/ም የካቲት 19 ተመስርቷል ብለናል። የትግራይ ህዝብ ደግሞ ከፀረ ደርግ ስርአት ያደረገው አስከፊና መራራ ትግል አልረሳውም ነበር። ይሁን እንጂ በጊዜ ወያኔ ኢ.ህአዴግ ለሃገራችን ሊጠቅም እንደማይችል ስለታወቀ በህዝብ ትግል ከስልጣኑ ሊወገድ ይገባል በሚል ድምዳሜ ተደርሶበት የነበረው ወቅት ነው።

በምን አይነት የትግል መንገድ ይወገድ በፖለቲካ? ወይስ በትጥቅ ትግል,,,? የሚል በወቅቱ ከባድ ጥያቄ ነበረ። ትህዴን ድርጅት ግን የኢ.ህአዴግ ስርአት ሊወገድ የሚችለው በፖለቲካዊ ትግል ሳይሆን በትጥቅ ትግል ብቻ ነው በሚል የመጨረሻ ድምዳሜ የሚለውን አማራጭ ነው የደረሰው። ስለምን ድነው ? ሌላ አማራጭ ታጥቶ ነው,,? በመሰረቱ ግን ትጥቅ ትግል አስፈላጊና ወቅታዊ ሆኖ ተገኝቶ ነው,,,,?



ብስራት መፅሄት ለነዚህና ሌሎች አስመልክታ የትህዴን ድርጅት ከፍተኛ አመራር ከታጋይ መኮነን ተስፋይ አጭር ቃለ-መጠይቅ አካሂዳለች መልካም ንባብ።-

## <u>ቃለ-መጠይቅ ከታጋይ መኮነን ተስፋይ</u>

***ብስራት መፅሄት፡- እሺ ታጋይ መኮነን ተስፋይ፣ በመጀመሪያ ለዚህ ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ ፍቃደኛ በመሆንህ በመፅሄት ብስራት አንባቢያን ስም እጅግ አድርጌ ለማመስገን እወዳለው።***

*ታጋይ መኮነን ተስፋይ፡- እኔም በበኩሌ የመሰለኝን ሃሳብ እንዳካፍላችሁ የብስራት መፅሄት ተጋባዥ እንግዳ እንድሆን ግብዣ ስላደረጋችሁልኝ እጅግ ለማመስገን እፈልጋሎሁ።*

***ብስራት፡- ጥሩ ወደ ያዝኳቸው ጥያቄዎች ነው የምገባው እንደሚታወቀው ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ የደርግን ስርአት ለማስወገድ በተደረገው ለ17 አመት የቀጠለውን መራራ የትጥቅ ትግል ከፍተኛ ተሳትፎ ነበረው። ይሁን እንጂ ይህ ትግሉ ከተጨረሰ በኋላ፣ በአስር አመታት ውስጥ ድጋሜ ትህዴን በሚል ስም ትጥቅ ትግል ሊያደርግ ችሏል፣ ስለዚህ ህዝብ ከትግል ወደ ትግል ሊያሸጋገረው የቻለው ምክንያት ምንድ ነው? የዚህን ትግል አስፈላጊነትስ እንዴት ነው የምትገመግመው?***

*ታጋይ መኮነን ተስፋይ፡- ሁላችን እንደምናወቀው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ የደርግ ስርአት ከመምጣቱ በፊት ይሁን በደርግ ጊዜ የከፋ ችግር ነው*

የነበረው። ህዝብ ሰብአዊ መብቱን ተገፎ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የተባለው ተጠቃሚነት አልነበረውም። በስደት ላይ ሲንከራተት ብሎም በበሽታ ወድቆ፡ መብቴን ያለውም ጭምር እየተጨፈጨፈ፣ እየታሰረ፣ በመሳፍንትና በጨቋኞች ሲገረፍ ነበር። ለዚህ ችግር ለማስወገድ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የህይወትና የንብረት መስዋእት አድርጎ ደርግን ለማስወገድ ተረባርቦ በመታገል ስርአቱን ሊወገድ እንደሚገባው ያደረገ ህዝብ ነው።



የትግሉ አላማም ዲሞክራስያዊና ሰብአዊ መብቱ ለማስከበር፣ የህዝብ እኩልነት እንዲረጋገጥ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍትህ ለማግኘት ነበር። በዛን ጊዜ ህወሓት "ከደርግ ውድቀት በኋላ በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላም አስተማማኝ ዲሞክራሲና እኩልነት ይረጋገጣል" ይል ስለነበር። ህዝቡ ደግሞ ይህ እውነት ነው ብሎ አምኖ ተቀብሎ፡ የደርግ ስርኣት ለማስወገድ አቅሙን አሟጦ ታግሏል።

ይሁን እንጂ ከደርግ ስርዓት ውድቀት በኋላ ወያኔ ኢህአዴግ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ ሳይውል ሳያድር የህዝብን አደራ ሲክድ ስልጣኑን በአስተማማኝ ከጨበጠ በኋላ ህዝቡን ዞር ብሎ ሊያየው አልቻለም። በመላ አገሪቱ ግለኝነት፣ አድልዎ፣ የስራ አጥነትና ሌሎችም ማህበራዊ ችግሮች ከመስፋፋታቸው ውጭ እስከአሁን ድረስ ፍትህ ሊረጋገጥ አልቻለም። መስዋእትነቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ እኩልነት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ ተብሎ የተከፈለ እንጂ በደርግ እግር ሌሎች አስመሳዮችን ስልጣን ላይ ለመውጣት አልነበረም። ሆኖም ጥቂት ሰዎች ስልጣኑን ከህዝብ በሃይል በመንጠቅ ተቆጣጠሩት። መብቱን ለማስከበር የጠየቀ ይታሰራል፣ ፍትሕ የጠየቀ ይታሰራል፣ የልማት ተጠቃሚነትና እኩልነት ይኑር ያለም ቢሆን ይታሰራል ይንገላታል።

ከዚህ በመነሳት ስርዓቱ ወደ አምባገነንነት በመቀየሩ ፍትሃዊ አስተዳደር ሊያነግስ እንደማይችል፡ በስርዓቱ ስር ሆኖ ፖለቲካዊ ትግል ማካሔድ ደግሞ ተስፋ የሌለው መሆኑና በጠመንጃ ሃይል ካልሆነ በስተቀር ወያኔ በሰለማዊና ፖለቲካዊ ትግል ስልጣኑን ለሕዝብ የማያስረክብ መሆኑን ከተገመገመ በኋላ ዳግም የትጥቅ ትግል ለማካሔድ የሚያስገድድ ሁኔታ ሊፈጠር ቻለ።

ስለዚህም በ17 ዓመታቱ የትጥቅ ትግል ወቅት መልስ ያላገኙ የህዝብ ጥያቄዎች ለመመለስ የወያኔን ስርዓት በትጥቅ አስወግዶ ፖለቲካዊ ስልጣኑ የህዝብ እንዲሆን ለማድረግ በየካቲት ወር1993 ዓ/ም የት.ህ.ዴ.ን የትጥቅ ትግል ተመሰረተ። በአጠቃላይ የትህዴን የትጥቅ ትግል መነሻ የትግራይ ህዝብ ጭቆና ነው፤ መነሻው የወያኔ ክህደትና በህዝብ ላይ እየደርሰ ያለው ግፍና መከራ ነው። የትጥቅ ትግል አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም የሚል ጥያቄ የሚያምታታና እንደጥያቄም መነሳት ያለበት ጉዳይ አይመስለኝም። አስፈላጊ ነው በሚል ነው መረዳት ያለብን። ምክንያቱም የወያኔ ኢህአዴግ ስርዓት በሚያምንበት የትጥቅ ትግል መወገድ ስለሚገባው።

**ብስራት፦ እሺ ጓድ መኮነን ይህ ትግል የስርዓቱ ክህደትና ግፍ የወለደው እንደሆነ ገልፀህልናል፣ ት.ህ.ዴ.ን የትጥቅ ትግል ሲጀምር በህዝብ የነበረው ተቀባይነትና ድጋፍ ምን ይመስል ነበር? በህዝብ ውስጥ ገብቶ ለመታገልስ እድል አገኘ ወይ?**

*ታጋይ መኮነን ተስፋይ፡- አዎ! መጀመሪያ እንደገልፅኩት የትግሉ መነሻ ጭቆና ነው። ድርጅቱ ሲመሰረት የሕዝብ ፍላጎት ምን እንደ ሆነ ገምግሞ ነው የተነሳው፡ ወያኔ በሃይል በዓመጽ ካልሆነ በስተቀር በሰላማዊና ፖለቲካዊ ትግል ሊወድቅ የማይችል መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የትግራይ ህዝብ ለውጥ የሚፈልግ መሆኑን ከተገመገመ በኋላ ነው ወደዚህ አማራጭ የተገባው። የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) የሚል ድርጅት የመመስረቱ ወሬ እንደተሰማ ህዝቡ ሳይውል ሳያድር ነበር ከድርጅቱ ጎን የተሰባሰበውና ሁለገብ ድጋፉን ማጠናከር የጀመረው።*

*የትህዴን ታጋይ በህዝብ ውስጥ ገብቶ ነው የሚሰራው፣ ሕዝብ ነው የሚያቅፈው፣ ጫካው ህዝብ ነው፣ በኢኮኖሚ በኩልም ድርጅቱ ሊቆም የቻለው ከህዝብ በሚያገኘው ድጋፍ ነው። የፖለቲካዊ እንቅስቃሴውም ቢሆን አብዛኛው የሚከናወነው በህዝብ አደረጃጀት ነው። በወታደራዊ ስራዎቻችንም ህዝቡ ስለ ጠላት መረጃ በመስጠት፣ መንገድ በመምራት፣ ቁስለኞችን በመንከባከብና ሌሎች የምንፈልጋቸውን ድጋፎች የምናገኘው ከህዝብ ነው። በህዝብ ድጋፍ ነው ስንሰራ የቆየነውና ያለነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ወጣቱ ትህዴን መመስረቱን ሲሰማ ከድርጅቱ ጎን ተሰልፎ አቅሙ በሚችለው ከትንሹ እሰከ ህይወቱ መስዋእት በማድረግ፡ በኢትዮጵያ ለውጥ ለማምጣት በርካታ ወጣቶች ወደ ትግሉ ጎራ ተቀልቅለዋል። ከዚህም የተነሳ ትህዴን በአጭር ጊዜ ለውጥ አሳይቷል። ይህም በህዝቡ ጠንካራ ድጋፍ የተገኘ ነው።*

*ይህ ድርጅት በአገር ውስጥም ይሁን ከአገር ውጭ ጠንካራ የህዝብ ድጋፍና ተቀባይነት ያለው ድርጅት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ከድርጅቱ ጎን ተሰልፎ ከፍ ያለ መስዋእትነት በመክፈል ወያኔን በመቃወም ሲታገል ቆይቷል። አሁንም በመታገል ላይ ይገኛል። ህዝባችን ለውጥ ፈላጊ ነው። የወያኔ ስርአት ከኢትዮጵያ እንዲወገድ የማይፈልግ ህዝብ የለም። ስለሆነም ወያኔ ኢህአዴግ ከአገር መወገድ አለበት። ወያኔ ሰማእታትን ክዷል። የህዝብ አደራንም በልቷል። የኢትዮጵያን ህዝብ እርስበርሱ እንዲጋጭ እድርጓል። ይህ ሁሉ ወንጀል የፈፀመ ስርዓት መወገድ አለበት። በመሰረቱ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ወያኔ ሲወገድ ነው እንጂ ወያኔ እያለ ለውጥ ሊመጣ አይችልም የሚል ወኔና ትክክለኛ ውሳኔ ስለ ያዘ ከድርጅቱ ጎን ተሰልፎ ለድርጅቱ እየደገፈ መጥቷል። የትህዴን ድርጅት በህዝብ ውስጥ የማይነቃነቅ የፀና መሰረት ሊተክል ችሏል። ስለዚህ የድርጅቱ እድገት የህዝብ ድጋፍ ውጤት መሆኑ መረዳት ይገባናል።*

***ብስራት፡- ጥሩ በአሁኑ ጊዜስ የድርጅቱ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ዓቅምና ጥንካሬ ምን ይመስላል ባጭሩ እንድትገልፅልን?***



*ታጋይ መኮነን ተስፋይ፡- አዎ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩልህ ትግል ትግል ነው! በትግል ላይ ትልቅ መስዋእትነት ነው እምትከፍለው። ይብዛም ይነስም በውስጥህም አንዳንድ ችግሮች ማጋጠማቸው አይቀርም። እየገጠምነው ያለነው ጠላትም ቢሆን ሌላ ተቀናቃኝ ሃይል ሊኖረው ስለማይፈልግ እንከኖች ሊፈጥር ይችላል። ከዚህም የተነሳ አንዳንድ ችግሮች አጋጥመውናል። አንዳንድ ወላዋዮችና ፀረ ትግል በድርጅቱ ላይ እንቅፋት ለመፍጠር*

እየሞከሩ መጥተዋል። ሆኖም ትግል ውስጥ ለውጥ ፈላጊው ስለሚበልጥ ድርጅቱ ድል እያደረገ የተሻለ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። በቅርቡም ያለፉት ክስተቶች ቅጥያ የሆነ ያጋጠመ ችግር ነበር። ለዚህም ችግር ድርጅቱ የድርጊቱ መነሻና እንደምታ ምንድነው ብሎ ጥልቅ ግምገማና ጥናት በማድረግ ለችግሩ ፖለቲካዊ መፍትሄ በማበጀት ድርጅቱ በአሁኑ ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ላይ ነው ያለው።

መሰረታዊው ነገር ትግል የሚጠይቃቸው ጉዳዮች አሉ። ትግሉ የሚጠይቀውን ነው የምትከፍለው። በተለይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ትግል የመጀመርያው አይደለም። በመግቢያችን ላይ እንደገለፅነው ደርግ ለመጣል የጠየቀውን ዋጋ ተከፍሏል። አሁንም ህዝቡ ወያኔን ለመጣል የሚጠይቀው ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጅቶ ነው እየታገለ ያለው። ድርጅታችን በአሁኑ ወቅት ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ዲፕሎማስያዊ ሁኔታዎቹን አስተካክሎ ካልፈው መድርክ ተምሮ ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያሸጋግር በሚያስችለው ሁኔታ ላይ ነው ያለው። ምክንያቱም ድርጅታችን ፈታኝ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የበለጠ እየጠነከረና እየተሻሻለ ነው የሚሄደው። በአሁኑ ጊዜም ድርጅታችን በአስተማማኝ መድረክ ላይ ሆኖ ብሩህ መፃኢውን እየተመለከተ ይገኛል።

**ብስራት፦ የሞላ አስገዶም የክዳት መንስኤ ምንድነው ትላለህ? ሞላ ይህንን አላማ ረግጦ ለመክዳት ያስገደደው ሁኔታ ምንድን ነው?**

ታጋይ መኮነን ተስፋይ፦ ምናልባት የሞላ ክዳት እንደ አንድ ዓብይ ርዕስ አንስተህ እንድትናገርለት የሚጋብዝ አይደለም። ጥያቄው ከተነሳ ግን መጀመሪያ ማየት ያለብን ሞላ ወደ ሊቀመንበርነት ደረጃ እንዴት ሊመጣ ቻለ የሚለውን ማየት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ከ1ኛው ድርጅታዊ ጉባኤ ጀምሮ ለዚህ ድርጅት ሊቀመንበር ሆኖ ይመራው የነበረ፡ ስውዕ ታጋይ ጓድ ፍስሐ ሃ/ማርያም በድንገት ሲሰዋ ከሁኔታው ጋር መጨናነቅ ነበር፡ ብዙ መረጋጋት አልነበረም። ስለዚህ ላጋጠመን መድረክ ጉባኤ እስከምናደርግ በጥገናዊ መንገድ ለመሸጋገር ነው የወሰንነው። በተደረገው የችኮላ 3ኛ ኮንፈረንስ ደግሞ ሞላ አስገዶም በጥገና መልክ እስከ ጉባኤ ጊዜያዊ ሊቀመንበር እንዲሆን ተደርጓል። ስለዚህ የሞላ ወደ ሊቀመንበርነት ደረጃ መምጣት በአጭሩ ይህንን ይመስል ነበር።

ሆኖም ሞላ ወደ ኃላፊነት ከወጣ ጀምሮ ብዙ ችግሮች እየፈጠረ ቆይቷል፡ ለዚህ ድርጅት እንደሚፈለገው ሊመራውና ሊያንቀሳቅሰው አልቻለም። ለሚፈጥረው ችግር መንስኤው ምንድን ነው ተብሎ ጥናት ሲደረግ፡ መሠረታዊ የአቅም እጥረት ወይ ማነስ መሆኑ ግልፅ ሆነ። አመራሩም በዚህ መንገድ ገመገመው፡ ችግሩ ይህ መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ አገዝ ስለሚያስፈልገው እስከ ጉባኤ እየታገዘ እየሰራ እንዲቆይ ተወስኗል።

ከጊዜ በኋላ ድክመቶችን እየበዙ ስለሄዱ በተባለው አገዝም ሊቀረፉ ስላልቻሉ፡ መሰረታዊ መፍትሄ ለማምጣት በአመራር ደረጃም ሆነ በአባላት ጉባኤ እንዲደረግ ተጠየቀ። ይህንንም ቢሆን ጉባኤው የማይቀር የሁሉም ታጋይ ወቅታዊ ፍላጎት መሆኑን ሲረዳ በጉባኤው በድርጅቱ ላይ ይፈፅመው በነበረ ጥፋት ከኃላፊነት ደረጃ ከሊቀመንበርነት ሊወርድ እንደሚችልና እንደሚጠየቅ አስቀድሞ ስላወቀ ጉባኤውን ለማዘግየት ነው የሞከረው።

ይሁን እንጂ ግምገማና ጉባኤ ይደረግ የሚል የሰራዊት ጥያቄ ሲበረታ ጉባኤው እንዲደረግ ተወሰነ ግምገማውም ተጀመረ፡ በዚህ ደግሞ ብዙ ነቀፌታዎች ቀርቦበት ደካማ

*መሆኑንም ተገመገመ፡ በፈፀመው ጉድለት ከሃላፊነቱ የሚወርድና የሚጠየቅ መሆኑን ስለተገነዘበ ደግሞ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ብሎ ወደ ጠላት ሊጠጋ ነው የመረጠው።*

*ስለዚህ በጠቅላላ ሁኔታው ይህንን ይመስል ነበር። በመሰረቱ ግን ይሄ ድርጅት በአላማ እንጂ በግለሰቦች ስለማይመራ ከግለሰቦች መኖር ጋር የሚያያይዝ የለውም፡ ይህ መስመር ትክክለኛ መስመር፣ ይህ አላማ ትክክለኛ አላማ ስለሆነ፡ በመስመሩ ነው ያለው፡ ቀጣይም ይኖራል። የሞላ ክህደት በሚመለከት ግን መነሻው ይህ የገለፅኩልህ ነው።*

***ብስራት፦ እሺ ጓድ መኮንን ወደ ሃገራችን ሁኔታ ልውሰድህና፣አገሪቱ በምን አይነት ሁኔታ ነው ያለች ከተባለ ብዙ ነገር ሊነገር ይችላል፡ እንደ ነጥብ ግን የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብቶችን እስኪ እንይ፡ ህዝባችን በአሁኑ ጊዜ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተጠቃሚነቱ ምን ይመስላል? በአገሪቱ ዴሞክራሲ አለ ሊያስብል የሚያስችል ነገር አለ ወይ?***

*ታጋይ መኮንን ተስፋይ፦ በመሰረቱ ወያኔ ፀረ ዴሞክራሲ ነው። ትግላችንም ወያኔ ፀረ ዴሞክራሲና ፀረ ህዝብ መሆኑ አስቀድሞ ስለተገመገመ ነው ሊመሰረት የቻለው። ወያኔ ዴሞክራስያዊና ፍትሃዊ እንዲሁም የህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራስያዊ መብቶች የሚያከብር ቢሆንማ ኖሮ ወደ ትግል መውጣት ባላስፈለገንም ነበር። ነገር ግን ከአፈጣጠሩ ፀረ ዴሞክራሲ ስለሆነ ተገደን ነው የገባነው። ወደ ጥያቄህ ልመለስና በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የሚባል ነገር የለም፡ ሰብአዊ መብት የሚባል ነገር የለም። የኢትዮጵያ ህዝብ የተወያየባቸውና ያመነባቸው አጀንዳዎችና አስተሳሰቦች አይደሉም የሚተገበሩት። ከተፅእኖ ነፃ የሆነ የዳኝነትና የፍርድ ስርዓት እንዲሁም መልካም አስተዳደር የሚባል የለም።*




*ሃሳቡን የገለፀ ማንኛውም ሰው ይታሰራል ታስሮም ፍርድ አያገኝም። ተሰባስበህ ስለ አገርህ ጉዳይና ስለ ህዝብህ ጉዳይ ለመምከር ብትፈልግም ምን እያደርግክ ነው? ከየት ነው የመጣኸው? ፀጉረ-ለወጥ ነህ ወዘተ... እየተባለ ህዝቡ ይሰቃያል። ሰላዮች በብዛት በማሰማራት፡ ፌደራል ፖሊስ፣ መደበኛ ፖሊስ፣ ሚልሻና ሌሎች ታጣቂዎችን በገንዘብ በመደለል ህዝብን ከመጨፍጨፍና የህዝብ ድምፅ እንዳይሰማ ከማፈን ውጭ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሁሉም በእኩል አይን አይቶ የፍትህ አገልግሎት የሚሰጥ አካል የለም። ስርአቱ በቁጥጥሩ ስር በሚገኙ መገናኛ ሚድያዎች አማካኝነት ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዳሰፈነ ይገልፃል፡ ሃቁ ሲታይ ግን ወያኔ የሚላት ኢትዮጵያና እኛ የምናውቃት ኢትዮጵያ የተለያዩ ናቸው።*

*በአንዷት ዴሞክራስያዊት ሃገር ዜጎች መሪዎቻቸውን የመምረጥና የመመረጥ ዴሞክራስያዊ መብት አላቸው። በአገራችን እስከአሁን ድረስ በተካሄዱ አምስት የማስመሰያ ምርጫዎች ግን ህዝባችን ከሌሎች ጊዜያቶች በከፋ መልኩ በጅምላ ሲታሰርና ሲጨፈጨፍ እንዲሁም ሲጨናነቅ ነው የሚታየው። በምርጫ ወቅት የሰራዊትና የመሳርያ ትርምስ ነው የሚበዛው። ይህ ደግሞ የስርአቱ ፀረ-ዴሞክራስያዊ አካሄድ የሚያጎላ ነው። በአጠቃላይ ስርአቱ እስካሁን ድረስ በመሳርያ ሃይል በተፅእኖ ህዝብን እየጨፈጨፈና እያስፈራራ እያሰረና እየገደለ ነው ስልጣኑን ሊያራዝም የቻለውና በማራዘምም ላይ የሚገኘው። በዚህም የተነሳ*

በአሁኑ ወቅት ካለፉት ስርአቶች በከፋ መልኩ በህዝቦች መካከል ግጭቶችና አለመተማመኖች ተፈጥረዋል።

ቀጣይ የህዝብ ቅሬታዎችና ተቃውሞዎች አሉ። ሆኖም ስርአቱ በፍትህና በዴሞክራስያዊ አካሄድ የሚያምን ባለመሆኑ እኛ ባልንህ ብቻ ታዘህ ሂድ፣ ያልንህን ሰምተህ ሂድ፣ አድርግ ኣታድርግ ተብሎ ታፍኖ መተንፈሻ አላገኘም። በዚህም ምክንያት ችግሩ እየባሰ ሄዶ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ በርካታ አከባቢዎች ሰፋፊ የህዝብ ተቃውሞዎች እየታዩ ነው። በተለይም በ2008 ዓ/ም በትግራይ ክልል በመቀሌ፣ በማእከላዊ ዞን፣ በምእራባዊ ዞን፣ በሰሜናዊ ምእራብ ዞን በሽሬ እንዲሁም በወልቃይት በተቃውሞ አስተባባሪዎችና ተሳታፊዎች ላይ የሚደርሰውን አፈና ግድያና እስር ተቋቁመው የሚካሄዱ ተቃውሞዎች አሉ። ይህም የሚያሳየን ነገር ቢኖር ህዝቡ መጠኑ ባለፈ ጭቆናና አፈና የተማረረ መሆኑንና ህዝቡም ሲብስበት ሆ! ብሎ ተነስቶ ተቃውሞው እየተቀጣጠለ መምጣቱን ነው።

በኦሮምያ ክልል ከህዳር ወር 2008 ዓ/ም ጀምሮ እስከአሁን መቋጫ ያልተበጀለት ህዝባዊ ቁጣ ተነስቶ በመቶዎች የሚቆጠር የንፁሃን ዜጎች ህይወት በመቅዘፍ እየቀጠለ ነው። በደቡብና በጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም በአማራ ክልል በአማራና በቅማንት ብሄረ-ሰብ መካከል የተፈጠረው ትልቅ ግጭት የወያነ ኢህአዴግ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ባህርይ የፈጠረው ክስተት ነው። ህዝቡ አቤት! ብሎ የሚሰማው ሲያጣ ወደ አመፅ እያመራ ነው።

በአጠቃላይ የአገሪቱ የዜጎች የሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብት አያያዝ ብንመለከት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመሄድ ላይ ነው። ሰዎች ያለፍርድ ይታሰራሉ እስር ቤት ከገቡም በኋላ ዘወር ብሎ የሚያያቸው አጥተው ለአመታት የስቃይ ህይወት የሚያሳልፍ ህዝብ እጅግ ብዙ ነው፣ ስርአቱ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብት የማክበር ባህርይ የለውም። ለቀጣዩም ይኖረዋል ተብሎ ተስፋ የሚጣልበት ስርአት አይደለምና።

**ብስራት፡- በአሁኑ ግዜ በአገራችን ከጫፍ ጫፍ ሃይለኛ ተቃውሞ በመካሄድ ላይ ይገኛል፣ በተለይም ደግሞ በትግራይ ክልል ከአሁን በፊት ይህን ያህል ተቃውሞ አይታይም ነበር በአሁኑ ወቅት ግን በሰፊው መታየት ጀምሯል፣ የዚህ መነሻው ምንድነው? ከዚህ በፊት ከነበረው ሁኔታ ለየት ባለ መልኩ ተቃውሞዎችና ሰልፎች እንዲካሄዱ ያስገደደው ምክንያት ምንድነው? ምንስ የተፈጠረ አዲስ ነገር አለ ትላልህ? በተመሳሳይ ከወልቃይት ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚካሄድ ተቃውሞና ግርግር አለ የእነዚህ ምክንያት ምንድነው ትላለህ?**



ታጋይ መኮንን፡- መነሻው ጭቆና ነው፣ ምሬቱ እላዩ ላይ የተጫነው የጭቆና ቀምበርና ችግር ነው። በአሁኑ ሰአት የኢትዮጵያ ህዝብ ትዕግስት በተለይም ደግሞ የትግራይ ህዝብ ትዕግስት ስለተሟጠጠ ነው። አፈናና ጭቆናው እየከፋ በመምጣቱ የህዝብ ትእግስት ከዚህ በላይ ሊሄድ አይችልም። እላይ ለመግለፅ እንደሞከርነው ወያነ እስካአሁን ድረስ በመሳርያ ሃይል ስልጣን ላይ ቆይቷል፣ ህዝባችን በሃይል ገዝቷል፣ አሁን ግን ህዝቡ የስርአት ለውጥ ይፈልጋል፣ የስልጣኑ ባለቤት ሊሆን ይፈልጓል፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃና ፍትሃዊ የሆነ ስርአት እየፈለገ ነው።

ከአሁን በፊት በትግራይ እምብዛም ተቃውሞዎች አልነበሩም ብለኸኛል። በእርግጥ በገሃድ አይታይም ነበር እንጂ ተቃውሞዎች ስላልነበሩ አይደለም። የፀጥታ ሃይሎችን በብዛት በማሰማራት፣ አንድ ለአምስት፣ አንድ ቤት ለአስር ቤት በሚል አደርጃጀት እንዲሁም በፖሊስ በሚልሻና ገፋም ሲል በመከላከያ ሰራዊት ታፍነው ስለቆዩ ነው እንጂ ተቃውሞዎች ነበሩ።

በአሁኑ ወቅት ግን ህዝባዊ ተቃውሞው በሁሉም አከባቢዎች እየበረታ በመሄድ ላይ ስለሆነ ስርአቱ እንደበፊቱ ተቃውሞውን ሊያፍነው አልቻለም። ከአቅሙ በላይ እየሆነ ነው ጎልቶ የሚታየው። የትግራይ ህዝብ ለውጥ ይፈልጋል። እስካሁን በትግራይ ህዝብ ስም ብዙ ተነግዷል፡ ወያነ በበላው የትግራይ ህዝብ ሲመረርና ሲጠላ ቆይቷል። በአገር ውስጥም በጎረቤት አገሮችም ያልተሰማው የትግራይ ተወላጅ የለም። ከዚህም አልፎ በስራ እጦት ምክንያት በመሰቃየት ላይ የሚገኝ ህዝብ ነው። ስራ ቢገኝም በጉቦ፣ በአድልዎና በሙስና ነው የሚገኘው። የሚሰጥ የሌለው ወገንም ጦሙ በማደር ላይ ይገኛል።

የተከፈለው መስዋእትነት ግን የጥቂቶችን ጥቅም ለማረጋገጥ አልነበረም፡ ሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ በአንድነትና በእኩልነት ተጠቃሚዎች የምንሆንበት ስርአት ለመፍጠር ነበር። ይህ ግን እውን ሊሆን አልቻለም። ህዝባችን የሚነደፉት ስትራተጅዎችና መላምቶች የማይጨበጡ መሆናቸውን ስለተገነዘበ ከጫፍ ጫፍ በመነሳት ተቃውሞውን በማሰማት ለመብቱ በመታገል ላይ ይገኛል።



እላይ እንደገለፅኩልህ በትግራይ ክልል ብቻ በመቀሌ፣ ብዘት፣ አዲግራት፣ አክሱም፣ አድዋ፣ ሽሬ፡ እንዲሁም እስከ ሁመራ በተለያዩ ወቅቶች ተቃውሞዎች ተነስተው ነበር። በተለይም በሁመራ እስከ 300 የሚደርሱ የሞተር ሳይክል ባለ ቤቶች ተቃውሞ ያነሱበት ሁኔታ ነበር።

ይህም ብቻ ሳይሆን በኦሮምያ ክልል በዩኒቨርስቲዎች፣ በኮሌጆች በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለወራቶች የቀጠሉና አሁንም ያላባሩ ተቃውሞዎች ተነስተዋል። በሌሎች ስፍራዎችም በተመሳሳይ ብሄር ነክ ጥያቄዎች ተነስተዋል። የራስን መብት በራስ የመወሰንና ራሳችን በራሳችን መተዳደር አለብን የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ለነኝህ ሁሉ ከስርአቱ የተሰጠው መልስ በጠመንጃ ሃይል ማፈንና ዜጎችን በጠራራ ፀሃይ መጨፍጨፍ ነበር። የተቃውሞዎቹ መሰረታዊው መነሻ ደግሞ የወያነ ኢህአዴግ አስተዳደር ጥላቻ ነው። ራሱ ወያኔም ያመነበት ጉዳይ ነው።

ለ25 አመታት ሲከደው የነበረውን የስርአቱ ፀረ ዴሞክራስያዊ አካሄድ የፈጠራቸው ችግሮች በሙሉ **“በሌሎች ላይ እጃችን የምንቀስርበት ጉዳይ የለም ችግሩ የመልካም ኣስተዳደር እጦት ነው”** በማለት በአገሪቱ የተፈጠሩት ችግሮችና አለመረጋጋቶች መነሻቸው የመልካም አስተዳደር እጦት መሆኑን አምኖ ተቀብሏል። ይህም የህዝብ ተቃውሞና ግፊት ውጤት ነው።

ሌላው በትግራይና በአማራ ክልሎች መካከል በወልቃይት ምክንያት የተፈጠረው ችግርና ጥላቻ በወያኔ የአስተዳደር ችግር ምክንያት የተነሳ ነው። የወልቃይት ወረዳ ህዝብ የሚተዳደርበትን ክልል ለማማረጥ ስለፈለገ ሳይሆን ወረዳውን የማስተዳደርና በመሬቱ የመጠቀም መብቱ በመነፈጉ የተከሰተ ችግር ነው። የወልቃይት ወረዳ ወደ ትግራይ ወይም ወደ አማራ ክልል መጠቃለል የችግሩ መፍትሄ ሊሆን አይችልም። መሰረታዊው መፍትሄ

*ሊሆን የሚችለው በአገሪቱ ውስጥ የህዝብ እኩልነት የሚያረጋግጥ ፍትሃዊ የሆነ ስርአት መዘርጋት ነው። ይህ ደግሞ በወያነ ኢህአዴግ ስርዓት መቃብር ላይ ካልሆነ በስተቀር በወያነ አካሄድ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገበት አካባቢ መርጦ የመኖርና የመስራት መብቱ እንዲረጋገጥለት ከተፈለገ የተጀመረውን ህዝባዊ ትግል ማስቀጠል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።*

*ተቃውሞው በሁሉም የአገሪቱ አቅጣጫዎች እየተስፋፋ ነው። የከፋ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ደግሞ አብዛኞቹ ተቃውሞዎች ይዘዉት የተነሱት ጥያቄ የብሄር ጥያቄ በመሆኑ አደገኛ ነው። በጥንቃቄ ሊያዝ ካልቻለ ውሎ አድሮ አገሪቷ እንዳትበታተን ያሰጋል። እኔ የሚያሰጋኝ ይህ ጉዳይ ነው። ይህም ስርአቱ የፈጠረው ችግር ነው በመሆኑም ህዝቡ ስርአቱን ለመገርሰስ በመታገል ላይ ይገኛል። ይህም ስርአቱን በጫፍ ላይ እንዲገኝ ስላስቻለው የተቃውሞውን ግለትና አቅጣጫ ለማስቀየር የማይፈጥረው ምክንያት የለም።*

*የሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብት ጥያቄ ይዞ ወደ ተቃውሞ የወጣ ህዝብ አሸባሪዎች ያቀነባበሩት ለማስመሰል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ማንኛውም ሰው ሃሳቡና ተቃውሞው በሰላማዊ ሰልፍ የመግለፅ መብት አለው። ይህን ጉዳይ ከአንዳንድ አሸባሪዎችና ተቃዋሚዎች ጋር በማያያዝ ተጨባጭን ሁኔታ የማይገልፅ ስሞችና ትርጉሞች በመስጠት የህዝብ ጥያቄን ለማፈንና ለማኮላሸት መሞከር የአንድ ዴሞክራስያዊ ስርአት እገነባለሁ የሚል ስርአት መገለጫ አይደለም።*

*በአጠቃላይ ስናየው ህዝብ ተቃውሞ ሊያካሂድና እያንዳንዱ እንዲከፋፈል የሚያደርገው ራሱ ወያኔ ነው፡ በተቃራኒው ደግሞ የችግሩ ጠንቅ ወያኔ መሆኑ አውቆ በወያኔ ላይ እየተነሳ ነው። አብዛኛዎቹ የሚካሄዱት ተቃውሞዎች ካየናቸው የወያኔን ጥላቻ መነሻ ያደረጉ ናቸው፡ አብዛኛው ህዝብ ደግሞ ፖለቲካዊ ትግሉ ሰልችቶት ወደ አመፅና ወደ ጠመንጃ ሃይል እያመራ ነው። ዶማ ብረት ሌሎች ብረታ ብረቶች በመያዝ እስከ አፍንጫው ከታጠቀው ሰራዊት ጋር በመግጠም እየተዋጋ ነው።*

*በኦሮምያ፣ በሶማል፣ በአማራ በትግራይም እንደዚሁ ወያኔ ወደ ሚወገድበት አቅጣጫ በማምራት ላይ መሆኑን እያየን ነው። በየትኛውም መልክና መንገድ ለሚለው ጥያቄ የራሱ የሆነ መፍትሄ ሊኖረው ነው፡ አጠቃለህ ስታየው ውጤቱ የወያነ የተበላሸ አስተዳደር መሆኑ ልንረዳው ይገባል፡ በጠቅላል አገሪቱ ወያነ እንደሚገልፀው በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ የተረጋጋች ሰለማዊ አገር ሳትሆን እየተደነባበሩ ወዳልተፈለገ መንገድ እየሄዱ ፖለቲካዊ መረጋጋት የሌለባት አገር ሁናለች።*

***ብስራት፦ በኢኮኖሚ ዘርፉ ስንመጣስ የአገሪቱ ይሁን የህዝቦቿ የኢኮኖሚ ሁኔታስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል ትላለህ?***

*ታጋይ መኮነን ተስፋይ፦ በመጀመርያ ደረጃ በአገሪቱ ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍልና ተጠቃሚነት የሚባል ነገር የለም። ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍልና ተጠቃሚነት ካለ አንዱ በይ አንዱ ተመልካች ስለማይሆን የኑሮ ደርጃው ዝቅተኛ ቢሆንም አምስግነህ ልታድር ትችላለህ። እኩል የሆነ የሃብት ክፍፍልና ተጠቃሚነት ከሌለ ግን ሁለት ሕብረተሰብ ይፈጠራል። ጥቂት ግለሰቦች ከመጠን በላይ ሃብት አካብተው የተቀናጣ ህይወት ሲመሩ ብዙሃኑ የበይ ተመልካች ሆነው ይቀራሉ።*

ወደ አገራችን ሁኔታ ስንመጣ ከስርአቱ ጋር ቅርበት ያላቸው ወይም የሚተርፍ ገንዘብ ኖሮአቸው ጉቦ ሊሰጡ የሚችሉ ጥቂት ግለሰቦች ካልሆኑ በስተቀር፡ አብዛኛው ህዝብ በከፋ የኑሮ ደረጃ ላይ ነው ያለው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የተዳከመ በመሆኑ የዕለት ጉርስ አጥቶ አንጀቱ ታጥፎ ውሃ ጠጥቶ የሚያድርና ለልመና ጎዳና የሚወጣ ህዝብ ጥቂት አይደለም።

የዚህ ችግር መነሻ ደግሞ አገሪቱ ለ25 ዓመታት ያህል የተከተለችው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው። አገሪቱ ወደከፋ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት በማምራት ላይ ናት። ይህም አጠቃላይ ስርአቱ የሚከተለው የተሳሳተ አከሄድ ውጤት ነው። የኛ ግምገማ ይህ ነው። በመሰረቱ ግን አንድ ማየት ያለብን የፖለቲካ ነፃነትን የማይፈቅድ ስርአት የሃገር የኢኮኖሚ አርነት፣ የዜጎችዋ ነፃነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ሊያረግግጥ አይችልም።



**ብስራት፡- ህዝቡ ከጫፍ ጫፍ በአመፅና መጨረሻ በሌለው ተቃውሞ ላይ መሆኑንና የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ በመዳከም ላይ መሆኑን ስትገልፅልን ቆይተሃል፣ ከዚህ በመነሳት የስርአቱ ተጨባጭ ሁኔታ እንዴት ልንገመግመው እንችላለን? ስርአቱስ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?**

ታጋይ መኮነን ተስፋይ፡- አንድ መታየት የሚገባው መሰረታዊ ነገር ቢኖር አንድ ስርአት ህልውናው ሊያረጋግጥ ከፈለገ በህዝብ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል። በመጀመርያዎቹ ግዜያት ህዝቡ ወያኔ ኢ.ህአዴግ ፍትሃዊ ድርጅት ነው፡ በከፈልነው መስዋእትነት ሰላምና ዴሞክራሲ እናገኛለን የሚል ምኞትና ሃሳብ ነበረው። ይህን አምኖም ነበር ለትግሉ የሚያስፈልጉትን ከንብረቱ ጀምሮ እስከ ህይወቱ መስዋእት የከፈለው። ሆኖም ድርጅቱ ስልጣን ከተቆጣጠረ በኃላ ከህዝብ እየተራራቀና እየተነጠለ ነው የመጣው። ከዚህ ሁኔታ በመነሳትም ስርአቱ በሃይልና በማታለል ረግጠህ መግዛት የሚል ስልት መከተል ጀመረ።

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የምርጫ ወቅት ሲደርስ ብዛት ያላቸው ፖሊሶች፣ ሌሎች ታጣቂዎችና ስውር የደህንነት ሰዎችን በማሰማራት ኢ.ህአዴግን ካልመረጣቹ እያሉ ነው ህዝቡን እሚያስፈራሩት። ኢ.ህአዴግን ካልመረጥክ መታወቂያህ ትቀማለህ እያሉ ያስፈራሩዋቸዋል። የወያኔ ካድሬዎች እስከ ቀበሌና ጎጥ እየወረዱ ነው ህዝቡን የሚያስፈራሩት ይህም ስርአቱ ምን ያህል ከህዝብ እንደተነጠለ ነው የሚያሳየን።

ውስጣዊ ሁኔታውም ቢሆን የተረጋጋ አይደለም። እርስ በርስ ያለመስማማትም ይታያል። ይህም በቅርቡ በተካሄደው የህወሓት ጉባኤ ላይ ተንፀባርቋል። ህወሓት ጉባኤ ያደርጋል ድክመቶች ይነሳሉ ግን አይስተካከሉም። ፀረ ሙስና የሚባል ተቋም አቋቁመዋል ሆኖም ይህ ተቋም ለራሱ በሙስና የተዘፈቀ ነው። በአጠቃላይ ህወሓት በመበስበሱ ስልጣኑን ለህዝብ ማስረከብ አለበት የሚሉ ተቃውሞዎች ከውስጡም ይነሱበታል። በገሃድ የሚወጡ ተቃውሞዎችም አሉ ቀደም ብሎ ብ1993 ዓ/ም ያጋጠመ መከፋፈልም መነሻው ይህ ነው። ስርአቱ ከድሮም ጀምሮ ውስጣዊ ሰላም የለውም።

ደርግን ለመጣል በተደረገው ትግል ታጋዩ ደሞዝ አልነበረውም። ደሞዙ መጪው ብሩህ ራኢ.ው ነበር፡ ከተሰዋሁ ለህዝቤ ከተረፍኩም እራሴንና ህዝቤን እጠቅማለሁ ብሎ ነበር። ሆኖም ከድሉ ማግስት ግለኝነት ተስፋፍቶ እኩሉ ከአቅሙ በላይ ሲበላ እኩሉ ደግሞ የበይ ተመልካች ሆነ። በበይና በተመልካች መካከል ያለው ልዩነትም ሰፊ ስለሆነ በስርአቱ ውስጥ በቀጣይነት የሚነሱ ያለመስማማቶች አሉ።



በሰራውዊቱም ውስጥ የሚነሱ ተቃውሞዎች አሉ። ብዙ መሳርያዎችና ጥይቶች ይሸጣሉ። በአጠቃላይ የስርአቱ ውስጣዊ ሁኔታ እየተዳከመና እየተበላሸ የሚተማመንባቸው ካድሬዎች ሳይቀሩ እየተቃወሙትና እየከዱት ሄደዋል። በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ያለው ህዝብም ከጫፍ ጫፍ በስርአቱ ላይ ተነስቷል። የህዝቦቻችን አብዛኞቹ ጥያቄዎች ደግሞ ወያኔ ኢ.ህአዴግ ከስልጣኑ ይነሳልን የሚሉ ናቸው። ይህም የሚያሳየን ነገር ቢኖር ወያኔ ከህዝብ ተነጥሎ ብቻውን ገደል አፋፍ ላይ መሆኑን ነው።

ወያኔን የማያብጠለጥልና የማያማ ሰው የለም፡ ኢ.ትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ሊመጣ ከተፈለገ ወያኔ ኢ.ህአዴግ ስልጣኑን ለህዝብ ማስረከብ አለበት፡ የወያኔ ህገመንግስት መስተካከል አለበት፡ ህዝብ ሊወያይበትና ሊያምንበት ይገባል። በቃላቶች እየተሸነገልን ለውጥ በሌለው ጎዳና መጓዝ የለብንም የሚል ጥያቄ ከስርአቱ ትላልቅ ካድሬዎች ጀምሮ ህዝቡ በሞላ እያነሳው ነው።

የኢ.ህአዴግ ስርአት እንደቀድሞው ህዝቡን በሃይልና በተፅእኖ ብሎም በሚድያ በማምታታትና በገንዘብ ሃይል የህዝብ ጥያቄዎች በማዳፈን ካልሆነ በስተቀር በውስጡ ስለጠነከረና በህዝቡ ተቀባይነት ስላገኘ አይደለም እስከአሁን የቆየው። በህዝቡም ይሁን በካድሬዎቹ የነበረው ተቀባይነት እየተሟጠጠ በመሄድ ላይ ስለሆነ የስርአቱ ውድቀት አይቀሬነት የተረጋገጠበት ሁኔታ ላይ ነው ያለነው።

**ብስራት፡- ከድርጅታችን አላማዎች አንዱ በኢ.ትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት ከሚያምኑ ድርጅችና ግለሰቦች ጋር ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል፡ ከዚህ አንፃር አሁን ከተቃዋሚዎች ጋር ያለን ዝምድና ምን ይመስላል?**

ታጋይ መኮነን ተስፋይ፡- ወያኔ ኢ.ህአዴግ የኢ.ትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ እንዲጠራጠርና እንዳይቀራረብ አድርጓል። የትጥቅ ትግልም ይሁን ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል



በሚያካሂዱ ተቃዋሚ ድርጅቶች መካከልም ጥሩ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ብዙ ሰርቷል። የድርጅታችን አቋም ግን ተራርቀህ የሚመጣ ለውጥ አይኖርም የሚል ነው። ልዩነታችንን በማጥበብ ተቀራርበን በመፍታት ምን ላይ ነው የምንለያየው ምንስ ላይ ነው የማንለያየው የሚለውን በመለየት እንዴት መፍታት እንችላለን የሚል እንደ አንድ ስትራተጂ ይዞ ነው የተነሳው። በትብብር ለመስራት ለኢ.ትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት መስዋእት መክፈል አለብን የሚል ነው። ችግር ካላቸው ድርጅቶችም ጋር ቢሆን ችግሩ ተቀራርበህ ነው መፈታት ያለበት የሚል ፅኑ እምነት

አለው። በዚህም አቋም ከላይኛው የድርጅቱ አመራር እስከ ታችኛው አባል አንድ አይነት አረዳድ አለው።

ከዚህ በመነሳትም በ2000 ዓ/ም የተካሄደ የአራት ድርጅቶች ጥምረት ነበር ድርጅቶቹም ት.ህ.ዴ.ን፡ ኢ.ህ.አ.ግ፡ ቤ.ህ.ነ.ን፡ ደ.ህ.ፍ.እ.ግ ሆነው በቋንቋና በባህል ብንለያይም ደማችንና አስተሳሰባችን አንድ የሆነ፣ አንድ ጠላት ያለን የአንድ አገር ዜጎች መሆናችንን ግምት ውስጥ በማስገባት የተካሄደ ጥምረት ነበር።

ጥምረቱ በየጊዜው እየተጠናከረ ነው የሄደው። እላይ እንደገለፅነው ጥምረቱ በአራት ድርጅቶች የተጀመረ ሆኖ በአሁኑ ግዜ ሰባት ድርጅቶች ያቀፈ ሊሆን በቅቷል። ድርታችን አሁን በጥምረቱ የተካተቱና የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኙትን ድርጅቶች ልዩነታቸውን አጥበው አላማቸውን እንዲያሳኩና ለህዝብ እንዲያስተዋውቁ ከፍተኛውን ድርሻ ተወጥቷል።

ይህ ደግሞ እስከ ህይወት መስዋእትነት የደረሰ ከፍተኛ የጉልበትና የንብረት መስዋእትነት የጠየቀን ጉዳይ ነው። ጥምረቱን በማወሃሀድ በኩል የድርጅታችን አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደነበር ጠላትም ወዳጅም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ለቀጣይም ይህን አካሄድ ነው የምናምነውና የምንከተለው። ተራርቀህ የሚፈታ ችግር የለም ወያኔ የፈጠረው ችግር በመቀራረብ ነው የሚፈታው። በህዝቦች መካከል የተፈጠረው መቃቃር በጭቁኖች ትግል ነው ወደ ቀድሞው መመለስ የሚቻለው።

አንዲት አትዮጵያ ልትገነባ ከሆነ እኛ እንደ ኢትዮጵያውያን ህዝብ ይሁን ተቃዋሚ ድርጅቶች በአንድ እንደምንሰምር ነው የምናምነው። በአቋማችንና በፕሮግራማችን ሰፍሮ ያለው እየሰራንበትና መስዋዕት እየከፈልንበት መጥተናል። ለቀጣይም በሚያስማማን እየተስማማን፡ በማያስማማን ደግሞ ወደፊት መስማማት እንዳለብን፡ የሚያለያየን ምንድን ነው እየተወያየን ልንሄድበት የምንችል፡ ልዩነት ፈጥረዋል የሚባሉትን ድርጅቶች ሳይቀር ማለትም የመገንጠል ጥያቄ የሚያነሱ ድርጅቶች ከመራቅ ይልቅ ችግራችሁ ምንድን ነው ብለን መቅረብ፡ አይሆንም ኑ ግቡ ይህች አገር መበታተን የለባትም፡ ፍትሃዊ መንግስት ካገኘ መገንጠል የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ የለም። በእርግጠኝነት የድርጅታችን አቋም ይህ ነው በመገንጠል አናምንም። ስለዚህ ለኢትዮጵያ አንድነት በአቅማችን ስንሰራ ቆይተናል፡ በቀጣይም እንሰራበታለን።

***ብስራት፦ በመጀመሪያ ውይይታችን እንደገለፅክልን ትህዴን ድርጅት ከሚመሰረት ጀምሮ በጠላት ይሁን በአንዳንድ የትግል አድሃርያን የሚያጋጥሙትን እንቅፋቶች እየፈታ መጥቷል፡ ባለፈው ዓመት ላጋጠመው የድርጅቱ ሊቀመንበር ክዳትም እንደአመጣጡ ፈትቶት በጥሩ መድረክ ነው ያለው ። ከዚህ በኋላስ የትህዴን ድርጅት ጉዞ ወደ የት አቅጣጫ ነው ትላለህ?***

ታጋይ መኮነን ተስፋይ፦ አዎ ይህ እያጋጠመን የመጣው እየገለፅነው መጥተናል። በትክክል ሁል ጊዜ መድረክ ሊያጋጥም ባህርያዊ ነው። ልክ የተፈጥሮ ፀሃይ ከፈለቀች መጥለቋ ስለማይተርፍ፡ ወይም በጋ ከመጣ ክረምት መግባቱ ስለማይተርፍ የድርጅታችን ህይወትም እንደዚህ አድርገን እንውሰደው። አንድ ትግል ከተጀመረ ጥያቄው የዴሞክራሲ ጥያቄ፣ የሰላም ጥያቄ፣ የመብት ጥያቄ ስለሆነ የግድ ከግቡ ይደርሳል። በማንኛውም ታምር ይህንን ጉዞ ሊያግት የሚችል ኃይል የለም። ይህንን ልታደርግ ግን የራሱ የሚጠይቃቸው ዋጋዎች አሉ መስዋዕት አለ፣ ስንክልና አለ፣ ውጣ ውረድ አለ፣ በውስጥም አንዳንድ የሃሳብ ልዩነት ሊፈጠሩ የግድ ባህሪያዊ አድርገን እንውሰደው። ስለዚህ ድርጅታችን ተደጋጋሚ

እንቅፋቶች እያጋጠመው እንደመጣ ሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው። ከዚህ መድረክ ግን እየተሳለ እየጠነከረ ነው የመጣው።

ይህ የምንገጥመው ጠላትም ራሳችን ያሳደግነው፣ ራሳችን ስልጣን የሰጠነው ነው። ስለዚህ ይህ ስርዓት በህዝብ ነው የወጣው አሁንም በህዝብ ትግል ነው የሚወርደው። ምናልባት አንዳንድ የማይረቡ ራስ ወዳዶች ከሃዲዎችና አፈግፋጊዎች እያጋጠሙን መጥተዋል። በእንደዚህ አይነቱ ግን መደናገር ነው የሌለብን፡ እንደገና ልንሞረድ፣ ብልህነታችን ሊጨምር፣ ከፍተኛ ሃላፊነት ልንሸከም፣ እኔ ምንድን ነው የሚጠበቅብኝ የሚል ነገር ነው ሁሉ ታጋይ ሊያስብበት የሚገባው፡ እምነታችን ምን ላይ ነው መሆን ያለበት…?



በአላማው፣ በፕሮግራሙ፣ በቀና መስመሩ ነው መሆን ያለበት፡ ግለሰብ ዛሬ ካለ ነገ ላይኖር ይችላል። የድርጅቱ አላማና ፕሮግራም ግን የሚቀየርና የሚለወጥ ሊሆን አይችልም። ይህ ታልፎ ተመክቶ አብቅቷል። ሞላ ጥቂት ሰዎችን አደናግሮ የህዝብን ትግል ረግጦ ወደ ወያኔ ስለገባ ወያኔ ደሞክራሲ ፌጥሯል ማለት አይደለም፡ የነበረው ግፍ፣ ጭቆና፣ ድህነት እዛው ከቦታው አለ።

ምናልባት ትግሉ ዓርብ ማለቅ የነበረበት ወደ ቅዳሜና እሁድ ሊሸጋገር ይችል ይሆናል። ዞሮ ዞሮ ግን ህዝብ ፍትህ፣ ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደር እየናፈቀ ስላለ ይህ እስካልተመለሰ ትግሉ ሊቋረጥ አይችልም። ስለዚህ ድርጅታችን ችግሮች ቢያጋጥሙትም ገምግሞ አይቶ እየተሻገራቸው መጥቷል። ከዚህ በኋላ ለሚያጋጥሙ ችግሮችም በተመሳሳይ የሚያልፋቸው እንደሆነ ነው የምናምነው። ስለዚህ የትህዴን ጉዞ የመጭው ብሩህ ተስፋ ነው፡ ግን ደግሞ የሚያኩራራ አይደለም፡ ጉባኤው የሚያስቀምጣቸው አሰራሮች ይሁን የተወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊ በማድረግ ተጋግዘህ ተነሳስተህ ለመስራት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው።

እነዚህ በተደጋጋሚ ለሚያጋጥሙት መድረኮች እየተሻገረ የመጣ ድርጅት ከዚህ በፊት ያልወደቀ ከእንግዲህ በኋላ ይወድቃል ይተርፋል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም መታለምም የለበትም። ይህ ድርጅት ችግሮች ምንድን ናቸው የሚያስተምር እንጂ በችግሮች የሚበረከክ ድርጅት አይደለም፡ ከዚህ በኋላ የሚመጡ ችግሮችም የቀለሉ እንጂ የከበዱ ሊሆኑ አይችሉም፡ ሁሉም ታጋይ በትግሉ ጉዞ የተሞረደ ነው። ስለዚህ በዚህ ድርጅት ጉዞ የተሻለ ብሩህና ግልፅ መፃኢ እንዳለ ነው ለእኔ የሚታየኝ፡ ወያኔም ከህዝብ እየተነጠለ ውድቀቱ እየተቃረበ እያሽቆለቆለ ነው እየሄደ ያለው።

ስለዚህ ለዚህ ተገኝቶ ላለው ለውጥ በማስጠበቅ ይዘነው ያለነው ትግል፡ ህዝቡም ጀምሮት ያለው የውስጥና የውጭ ተቃውሞ፣ በአገርና በበረሃ አጠናክረን መቀጠል ነው ያለብን። ስለ ድርጅታችን ግን ወዳጅም ይሁን ጠላት ማወቅ ያለበት ትህዴን ወደ ኋላ ሊመለስ በማይችልበት ሁኔታ ደርሷል፡ መሆን ያለበት ጥያቄ ድሉ ያጥራል ወይስ ይረዝማል የሚለው ብቻ ነው። ስለ ትግሉ ቀጣይነትና ህልውና የማያደራድር እንደሆነ ነው ላረጋግጥልህ የምችለው።

**ብስራት፦ እሺ ታጋይ መኮነን ተስፋይ፡ ትህዴን ሁለተኛ ድርጅታዊ ጉባኤ በማካሄድ ላይ ነው ያለው፡ በዚህ አጋጣሚ ይህንን አስመልክተህ ምን መልዕክት ልታስተላልፍ ትፈልጋለህ?**

*ታጋይ መኮነን ተስፋይ፦ ጥሩ መጀመሪያ አንድ መታወቅ ያለበት ድርጅታችን ትህዴን ይዞት የተነሳው አላማ ግልፅ፣ ፍትሃዊና ወቅታዊ ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ ያለው ችግር ሊፈታ ከሆነ ከትህዴን ጎን ተሰልፈህ ጠንክረህ መታገል ወሳኝ ነጥብ ነው። ይህ ድርጅት ደግሞ መስዋዕት እየከፈለ ነው የመጣው አሁንም ለነፃነት፣ ለሰላም፣ ለዴሞክራሲና ለፍትህ ስለ ህዝብና ስለሃገር መስዋዕት ለመክፈል ወደ ኋላ የሚልበት ምክንያት የለም። በመስዋዕቱ ደግሞ ሰላምና ዴሞክራሲ ሊያረጋግጥ እንደሚችል የሚያጠራጥር ነገር አይደለም። ስለዚህ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ከድርጅቱ ጎን በመቆም ለፍትህና ለሰላም መታገል አለበት፡ ጀምሮት ያለው ትግል ማጠናከር አለበት የሚል መልዕክት አለኝ።*



*በተለይ ወጣቱ ትውልድ ጠንክሮ ነው መታገል ያለበት፡ ብዙ ነገር ታያለህ ወጣቶች ወደ ስደት ሲጓዙ ለተለያዩ አደጋዎች ይጋለጣሉ፣ ይታረዳሉ፣ ኩላሊታቸውን ይሰለባሉ፣ ወታደሮች ሆነው በማይመለከታቸው በሶማሊያ ጉዳይ ገብተው ህይወታቸውን ሲያጡ ታያለህ፡ ስለዚህ ለዚህ ፀረ ህዝብ ስርዓት አገልጋዮች ከመሆን ነገ የታሪክ ተጠያቂ እንዳንሆን፡ ህዝቡ የስልጣን ተጠቃሚ እንዲሆን ከዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር ተሰልፎ መታገል አለበት። ስደት የችግር መፍትሄ አይደለም ይህ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ላስተላልፈው የምፈልገው መልዕክት ነው።*

*የትህዴን ታጋይ ደግሞ ስለድርጅቱ በመቆም ሌት ከቀን እየታገለ መጥቷል። አሁንም ይቆይልኝ ይደርልኝ የሚባል ጉዳይ አለመሆኑን፡ ለዚህ ሁለተኛ ድርጅታዊ ጉባኤ በድል አጠናቀን፡ ከጉባኤው በኋላ ላለው ሁኔታ ደግሞ በችግር ላለው ህዝባችን ነፃ ለማውጣት ሁሉም የድርጅታችን አላማዎች ለማሳካት መረባረብ እንዳለበት ነው መልዕክቴን የማስተላልፍ። በአጠቃላይ ግን ሁሉም አባላችንና ጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ ድርጅታችን በሚያስተማምን በተሻለ ሁኔታ እንዳለ የሚያጠራጥር ሁኔታ የለም። በጠላት ፕሮፖጋንዳ በጠላት የማይረባ ወሬ የሚደናገር ህዝብ መኖር የለበትም።*

*ወያኔ ለእሱ የሚቃወም ታጋይ ድርጅት እንዲኖር ባህሪው ስለማይፈቅድለት፡ አይደለም በትጥቅ ትግል በፖለቲካዊ ትግልም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል የኢትዮጵያ ህዝብ እራሱ ስለሚያውቀው ጠንክረንና ሃይለን ከድርጅታችን ጎን ሆነን ነው መታገል ያለብን፡ የሚያሸማቅቅ ነገር እንደሌለን ላረጋግጥልህ እፈልጋለሁ። በሁለተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን የነበሩንን እንቅፋቶች አስወግደን በድል እንቀጥላለን። ይህ የ2009 ዓ.ም ደግሞ ብሩህ የትግል ጉዞ እንዲሆንልን ነው የምመኘው፡ አመሠግናለሁ።*

***ብስራት፦ እሺ የትህዴን ከፍተኛ አመራር ታጋይ መኮነን ተስፋይ ያቀረብንልህን ጥያቄዎች ስለመለስክልን እጅግ በጣም እናመሰግንሃለን። ሁለተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ደግሞ ስኬታማና የተቀላጠፈ ይሆንልን ዘንድ ብስራት መፅሄት መልካም ምኞቷን ትገልፃለች፡ አመሰግናለው።***

# ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች

የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ድርጅት ከተመሰረተበት እለት ጀምሮ እስከ ዛሬ የሚታገልበትን አላማዎቹን ለማስተዋወቅና የጀመረዉ ህዝባዊ ትግል ተከታዮች አግኝቶ ወደ ድል እንዲደርስ አልሞ ሰፊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል። እነዚህ እስከ ዛሬ የተሰሩ የፖለቲካ ክንዋኔዎች መጀመሪያ ወደ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት የድርጅታችን የፖለቲካ ሰራዎች ለማሳካት በተደረገው እርብርብ ሁሉም ክፍሎች በሚመለከተው አኳኋን የድርጅቱ ፖለቲካዊ ስራዎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው።

ስለዚህ በእነዚህ በሁሉም መስመሮች በኩል በተካሄደው እርብርብ የድርጅቱ ታዋቂነት ከፍ እንዲልና በድርጅታችን ላይ ስህተት የሆነ አረዳድ የነበራቸው ጥቂት አካላት አስተሳሰባቸውን አሰተካክለው ከድርጅታችን ጋር በመተጋገዝ ለጋራ ጥቅም አብረው እንዲሰሩ በማድረግ ላይ ቀላል የማይባል ፖለቲካዊ ስራዎች ተሰርተዋል።

ትህዴን በአገራችን ያለውን ፀረ ህዝብ ስርዓት በህዝባችንና በአገራችን ላይ እያደረሰ ያለውን ግፎች ለማጋለጥና ለመታገል የፈፀማቸውን ወንጀሎች ለአለም ህብረተሰብ እንዲያውቃቸውና እንድያግዳቸው ለማድረግ በሬደዮ፣ በየካቲት ወለታ ቴሌቭዥን፣ በድርጅቱ ልሳን በሆነችው ብስራት መፅሄትና በwww.demhitonline.com በተሰየመ የመረጃ ድህረ ገፅ ከህዝብም ይሁን ከአለም ማሕበረሰብ ጋር እንደ መገናኛ መስመሮች ተጠቅሞ ለሚደረገው ትግል የሚያበረታቱ ስራዎች ተሰረቷል።




የተጠቀመባቸው አፈፃፀሞች ደግሞ በረጅም ፅሁፍ መልክ፣ በሀተታ፣ በመግለጫ፣ በአቋም፣ በቃለ መጠይቅ፣ በቪድዮ መልክ የተሰሩ ልዩ ዝግጅቶች፣ በዋናነት ደግሞ የድርጅታችን ልሳን የሆነችው ብስራት መፅሄት ከ23 በላይ እትሞች በተለያየ መንገድ የተለያዩ አምዶች ይዛ እንድትወጣ በማድረግ በወቅቱና በጊዜው ወደ ህዝብ እንዲደርስ በማድረግ ተግባር ላይ ረዥም ርቀት ተጉዟል። ከነዚህ ትላልቅ ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ ይገኙበታል።

- በቤልጀም የሌበር ፓርቲ አባል ከሆነው ጋዜጠኛ መሃመድ ሀሰን፣ ከግንቦት 7 ዋና ፀሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ ከብፁእ አቡነ መርቆርዮስ፣ የኢሳት ጋዜጠኛ መሳይ መኮነን፣ ከተለያዩ የትጥቅ ትግል ከሚያካሂዱ ተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮችና ከበርካታ ታላላቅ ተፅዕኖ ፈጣሪና ታዋቂ ሰዎች ጋር ስለ አገራችን የፖለቲካ ሁኔታ አስመልክቶ የተደረገ ግንኙነት፣
- በየወቅቱ የኢህአዴግ ስርዓትን እየተቃወሙ ወደ ትግል ከሚሰለፉ ሲቪሎችና የስርዓቱ ወታደሮች፣ በአስተዳዳሪነት ደረጃ ሆነው ለስርአቱ እያገለገሉ ከነበሩ ዜጎች ወቅታዊ የአገራችንና ህዝባችን ሁኔታ አሰመልክቶ ቃለ መጠይቅ በማደረግ ስርአቱን የሚከተለው ፀረ ህዝብ አካሄድ እንድያዉቅ አስችሏል።

እንዲሁም ከተለያዩ ተፀዕኖ ፈጣሪ ጋዜጠኞችና ታላላቅ ፖለቲከኞችን ጋር በመተባበር የድርጅታችን ውስጣዊ ሁኔታና ምንነት እየተካሄደ ያለውን ትግል የሚያስተዋውቁ የፖለቲካ መልእክት የያዙ ደኩሜንታሪ ፊልሞች ሰርቷል። የፖለቲካ ሃሳቦችንም ተለዋውጧል።



ጋዜጠኛ መሃመድ ሀሰን ለ8 ቀኖች ያክል የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታና የአለም ታሪክን አስመልክቶ ለፖለቲካ ፅፈት ቤት አባላት የፖለቲካ ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጓል።

በተጨማሪም በሁሉም ግንባር ባሉ የትህዴን ታጋዮች በመዞር ያካሄደው ግንኙነት ሰፊ የሆነ ዶክሜንታሪ ፊልም አዘጋጅቶ ወደ ቦታው ከተመለሰ በኋላ በትጥቅ ትግል ካሉ ድርጅቶች መካከል በመሬት ሲታይ የጠነከረ ድርጅት የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲዊ ንቅናቄ እንደሆነ ከኢሳት ቴሌቭዥን ጋር ባካሄደው ቃለ መጠይቅ ምስክርነቱን ገልጿል።



የኢሳት ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ መሳይ መኮነን ወደ ድርጅታችን መጥቶ ለብዙ ቀናት ዑደት በማድረግ በአይነቱ ልዩ የሆነ ዶክመንተሪ ፊልም ሰርቶ ውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በወቅቱ እንዲመለከቱት ተደርጎዋል። ስለ ድርጅታችን ብርታትና ጥንካሬ ምስክርነቱን ሰጥቷል። ማየት ማመን ነውና ሄዳችሁ እዩ ብሏል። ይህ ደግሞ የድርጅታችን ብርታትና ጥንካሬ በገለልተኛ አካላት የተመሰከረለት አጋጣሚ ስለሆነ በጥላቶቹ ላይ የፈጠረው ድንጋጤ ቀላል ነገር አልነበረም። ይህ ደግሞ ከድርጅታችን የፖለቲካ ተግባራት ውጤቶች አንዱ ነው።

ጋዜጠኛ መሀመድ ሀሰንና መሳይ መኮነን በሰራዊቱ ውስጥ ገብተው የሰሯቸው ዶክመንተሪ ፊልሞች ደግሞ በድርጅታችን የፎቶና ቪድዮ ባለሙያዎችና ችሎታ ባላቸው ኤዲተሮች በጥራት ተሰርተው እያንዳንዱ እስከ ሶሰት ሰዓት የሚደርስ ረጅም ጊዜ ያለው ፊልም ይዘው ሂደዋል። እነዚህ ቪድዮዎች ድርጅቱንን ከውጭ ህብረተሰብ ጋር ያገናኙ ትልቅ የፖለቲካ ስራዎቹ ናቸው።



ብፀእ አቡነ መርቆርዮስ በትህዴን በሚድያ ፅህፈት ቤት ተገኝተው ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ይህ በአገራችን ያለው ስርአት ለሁሉም ሃይማኖቶችና ተከታዮች የማያከብር ፀረ ሃይማኖት መሆኑን በመግለፅ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተባብሮ ለዚህ ስርአት እንድያስወግዱት ተማፅነዋል። ስለዚህ ይህ አባት ወደ ድርጅታችን መምጣት ራሱን የቻለ ፖለቲካዊ ኃይል ነው።



የግንቦት ሰባት ዋና ፀሀፊ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በበኩሉ የትህዴን ድርጅት አገራዊ ድርጅት እንጂ ጠባብ ብሄራዊ ድርጅት እንዳልሆነ አምኖ ድርጅቱ ከድርጅታችን ጋር ያለውን አጋርነት ለማረጋገጥ በአቅሙ ለማገዝ ለትህዴን ፖለቲካ ፅህፈት ቤት አባላት በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክቶ ሰፊ የሆነ የፖለቲካ ትምህርት መስጠት መቻሉ አንዱ የፖለቲካ ስራ ውጤት ነው።

የትህዴን ድርጅት በውስጥም በውጭም እስከ ምን ያህል ታዋቂነት እየያዝ እየሂደ እንደሆነ በሌሎች ሃይሎች እስከ ስንት ተፈላጊ እንደሆነ ያስመሰከረልን ደግሞ ከውጭ የመጡ ማርየና ኤልሳ የተባሉ ዜጎች የድርጅቱ የበላይ አመራር ጋር ግንኙነት ማድረጋቸው ነው። እነዚህ ሰዎች በታጋዮቻችን ካምፕ በመግባት ስለ ትህዴን ድርጅት ግንዛቤ ወስደዋል። ይህ ደግሞ የትህዴን ድርጅት እያካሄደው ያለው የህዝብ ትግል በተለያዩ አቅጣጫዎች ተከታዮችና ወዳጆች እያገኘ እንዳለ የሚያረጋግጥልን ፍፃሜ ነው።



ስለዚህ እነዚህ ለትግሉ ለማበረታታት ብሎ ወይም ለዚህ ትግል ለማየት የሚሹ በየወቅቱ መጥተው ድርጅታችንን አይተውታል። ኢትዮጵዊያን ብቻ ሳይሆን የውጭ ዜጎች ወደ ድርጅታችን መጥተው ሁኔታችንን አረጋግጠዋል። እስከ አሁን ደግሞ የድርጅቱን አመጣጥ በአወንታ ካልሆነ በመጥፎ ገልፀውት አይውቁም። ይህ ደግሞ የድርጅቱ አመጣጥ ወይም ደግሞ የድርጅቱ መሰረት ነው። አላማውና ፕሮግራሙ ቀና ስለሆነ በመጥፎ የሚያየን የለም። ይህንን አስተሳሰብ ለማምጣት የትህዴን ድርጅት ከባድ የፖለቲካ መስዋእትነት ከፍሏል።



ከዚህ አልፎ ትህዴን በባህልው ቡድን ታግዞ የመታገያ አላማዎችና ውስጣዊ እድገቱን ሲገልፅ፡ በህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው በደሎችና ግፎች የሚያጋልጡ በኢህአዴግ ስር እየተጨፈጨፈ ያለውን ህዝብ አንገቱ አቅንቶ መፍትሄ የሆነ አማራጭ አቅጣጫ የሚያመለክት ከ13 በላይ የታተሙ ካሴት ለህዝብ ዘርግቷል። ጎን ለጎን ደግሞ በአጠቃላይ የስቪል አባላትና ወዳጆቻችን የትግላችን ደጋፊዎቻችን "መን ዩጊላኺና ሃምበለይ" የሚል ሁለት ካሴት ሰርቶ አቀርቧል።

በባህል ቡድን በኩል የተለያዩ ይዘት ያላቸው ድራማዎችና ኮሜዲዎች በሬድዮ በቴሌቭዥንና በመረጃ ድህረ ገፅ በኩል ወደ ህዝብ እንዲደርስ በማድረግ የስርዓቱ ፀረ ህዝብ ተግባራቶቹን በመታገል ሰፊ ፖለቲካዊ ሰራዎች ተሰርቷ። ከስርአቱ ቁጥጥር ውጪ ላሉ ኢትዮጵያውያን በድርጅታችን ደጋፊ ማህበር አባልነት እንዲታቀፉና፡ በአቅማቸው ለድርጅቱ እንዲረዱ አድርጓል። ለምሳሌ የጠቅላላ ደጋፊ ማህበር የባህል ቡድን /የፅናት ባህል ቡድን/ ለድርጅታችን ፖለቲካዊ ስራ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።



ከዚህ ሌላ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራስያዊ ንቅናቄ /ትህዴን/ ድርጅት በስርአቱ ፀረ ህዝብ ተግባሮች በአገራቸው በሰላም ሊኖሩ ያልቻሉ በየወቅቱ ወደ ትግል የሚመጡ በርከት ያሉ የአገራችን ወጣቶች የድርጅቱን ፕሮግራምና ህግ በማስተማር በሌላ ወገን  በህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና በደል በጥልቀት አውቀው የፖለቲካ አስተሳሰባቸው እንዲያድግ  ስለ ህዝባቸውና አገራቸው ወኔ ታጥቀው እንዲታገሉ ለማደረግ ሰፊ የፖለቲካ ሰራ እየሰራ መጥቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅታችን በጋራ የሚደረግ ትግል ጠቀሜታውን በመረዳት እሱን ከመሰሉ ፀረ ኢ.ህአዴግ ከሚታገሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ያለውን ዝምድና ወደ ጥምረት ለማምጣት ጠንክሮ ተንቀሳቅሷል። ይህን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ በሚከተለው ርእስ እንመለከታለን።

## <u>የጋራ ክንድ ለማይቀረው ድል!!</u>

አገራች ኢ.ትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብት የበለፀገች የመሬት ገፀ አቀማመጥ ምቹና ተፈላጊ ብትሆንም  ህዝቡ ግን እስከ ዛሬ ጠግቦ ይሁን ሰላም አግኝቶ አያውቅም። ምክንያቱም እስከ ዛሬ በስልጣን ሲቀያየሩ የቆዩ ስርዓቶች ከአገራችንና ህዝባችን ጋር የሚስማማ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሊገነቡ አልቻሉም።

በዚህም ምክንያት የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ዘውትር በትግል ላይ ያለ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ግን ሃቀኛ ዴሞክራሲ፣ ቅንነት ያለው ስርአትና ፍትህ ልያገኝ አልቻለም። አገራችን የአመፀኞችና ግፈኞች መንደር ሁና ነው የቆየችው። የህዝበችዋ ትግልም ቢሆን እስካሁን ድረስ መቋጫ አላገኘም።

በአሁኑ ጊዜ በጠመንጃ  ሃይል የህዝብ ድምፅ አፍኖ ለሚቃወሙትና አንፃሩ ለሚነሱ ተቃውሞዎች ጨፍልቆ በስልጣን እየቀጠለ ያለ አመፀኛ ስርዓት ደግሞ  ከፅንሱ  ጀምሮ እስከ መጨረሻው ተንከባክቦ ያሳደገውና አሁን እስካለበት ደረጃ ያደረሰው የትግራይ ህዝብ ነው።

ስለዚህ የትግራይ ህዝብ ለህወሓት እንዴት እንደገነባው ስለ ምያውቀው እንዴት አድርጎ ሊያፈርሰው እንደሚችልም የሚያስቸግረው አይደለም። ስርዓቱም የትግራይ ህዝብ ትግል ከጀመረ ምን ልያደርግ እንደሚችል አሳምሮ ያውቀዋል።

ስለሆነም የህወሃት ማሌሊት ስርዓት የድርጅታችን ትህዴን መመስረት በከፍተኛ ነው ያደናገጠው። መድረኩ ደግሞ ለሁለቱም ድርጅቶች ለህወሓት ይሁን ለትህዴን የሞትና ሽረት መድረክ ሊሆን ባህርያዊ ነበር። ከዚህ የተነሳ ደግሞ ትህዴን ከተመሰረተበት እለት ጀምሮ የጀመረውን የትግል ጉዞ ለማኮላሸትና ከመሰረቱ ለመንቀል በጥላቶች ሰፊ ዘመቻ ተካይዶበታል።



ይህ ፍልምያ ግን በርግጥ ቅንነት ባላቸውና ቅንነት በጎደላቸው የተለኮሰ ስለ ነበረ ሃቅ የያዘ ሁሌ ስለ ምያሸንፍ ፅኑ አቋም ቅንነት የነበራቸው የትህዴን ታጋዮች አሸንፈው ሊወጡ ግድ ነበር። በጠላቶቹ የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ደግሞ ድርጅቱ ህይወት ዘርቶ እንዲሄድ አስችሎታል። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በፖለቲካዊ ህይወቱ የተረጋጋ፣ ውስጣዊ ሰላምና አንድነት ያለው፣ ፀረ ኢህአዴግ ጠመንጃ አንስቶ የሚታገል ድርጅት ሆኖ ይገኛል።

ይህ ድል ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ አይደለም። ድርጅታችን ትህዴን ህላዌነቱን አረጋግጦ ግዙፍ ዋስትና ሁኖ ለህዝቡ አለሁልህ እንዲለው የበቃ ከባድ የትግል ተግዳሮቶችን አልፎ ነው። ለገጠሙት ከባድ መሰናክሎች ከባድ ዋጋ ከፍሎ ነው ያለፋቸው። ዋጋ ሳትከፍል ድል እንደማይገኝም አሳምሮ ይውቀዋል። ድርጅታችን ትህዴን ገና ሲመሰረት ክቡር ኢትዮጵያዊ ማንነቱን የምያስመሰክርበት ንፁር የሆነ አላማ ይዞ ነው የተነሳ።

ከዚህ አንዱ ደግሞ የጋራ ጠላት በጋራ ለመደምሰስ በተባበረ ክንድ የምያምን የማይለወጥና የማይሸረሸር በአገር አንድነትና ሉዓላዊነት ከምያምኑ የትግል ሃይሎች ተቀራርበህ መስራት የሚል የፀና እምነት አለው። ይህ ደግሞ ገና ከጥዋቱ እየተገበረው መጥቷል።

ምክንያቱም ለጋራ ጠላት ተባብረህ በጋራ መስራት የጋራ ጥቅም ስለሆነ እኛም እንደ ኢትዮጵያውያን በጋራ ትግል በአንድነትና በመተጋገዝ ነው የምናምነው። ትግላችንም ለአንዲት ኢትዮጵያ ነው። አንዳንድ ወገኖች ግንዛቤ ከጎደለው አስተሳሰብ ተነስተው ስጋት ላይ ይወድቃሉ። ትላንት TPLF ነበር ዛሬ ደግሞ TPDM ምን ልዩነት አላቹሁ የሚል አስተሳሰብም አለ።

ነገር ግን ትህዴን እንደዚህ አይነት መሰረት የሌለው ከስጋት የሚመነጭ አስተሳሰብ ለአገራችን እንደማይጠቅማት በመረዳት የትግራይ ህዝብም ልክ እንደሌሎች ብሄሮች የተጨቆነ ህዝብ እንዲያውም ድርብ ጭቆና እያሳለፈ ያለ ህዝብ ስለሆነ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር ተባብሮ የሚሰራ መሆኑን እየገለፀ መጥቷል።

የዚህ ውጤትም ትህዴን በ16-03-1995 ዓ/ም በአውሮፓ ከኦነግ ጋር በአወንታ ሊነሳ የሚችል የመቀራረብ ውይይት አድርጓል። ይህ ድርጊት ደግሞ አንዳንድ ድርጅቶች በእኛ ላይ የነበራቸው አመለካከት እንዲቀይሩ በማድረግ ራሱን የቻለ አስተዋፅኦ ነበረው። ይህ በድርጅታችን በር ከፋች የሆነ ለጋራ ጥቅም የተደረገ የመቀራረብ ውይይት ነው።

ሌላ በ1998 ዓ/ም ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግምባር /ኢ.ህ.አ.ግ/ በምዕራብ በኩል ሁለት ጊዜ የጋራ ዘመቻ አካይደዋል። በ1999 ዓ/ም ደግሞ ድርጅታችን ትህዴን ሰፋፊ ወታደራዊ ዘመቻዎች የሚያካይድበት ወቅት ስለነበረ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች እዚህ ላይ ድርሻቸውን እንድያበረክቱ ለማድረግ ከፍተኛ ስራ ሰርቷል።

እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚጋባው ደግሞ የደቡብ ህዝቦች ፍትህና እኩልነት ግምባር "የህብረት ዘመቻ ለዴሞክራሲ" በሚል ስያሜ ያካሄደው የተሳካ ወታደራዊ ዘመቻ ነበር። ሁለቱ ድርጅቶች በጋራ ሆነው ለምዕራብ ትግራይ ህዝብ በማበሳበስ ላይ በነበረው የጠላት ሃይል ደምሳሽ የሆነ ሰፊ ወታደራዊ ጥቃት በማካየድ በጋራ መስዋእትነት ከፍለዋል።

ከዚህ በኋላ ትህዴን በጠባብ ብሄራዊ ስሜት የታጠረ አስመስለው ህዝብ በማወናበድ የነበሩ ወገኖች ሳይቀሩ ትህዴን ሰፊ አገራዊ ራኢ እንጂ ጠባብ ብሄራዊ አላማ እንደማይከተል በተግባር በመሬት ላይ ከሚሰሩ ድርጅቶች በጋራ ሊሰራ ዝግጁ እንደሆነ ያረጋገጡበት ዘመቻ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ ድርጅታችን በጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም ደግሞ ከዚህ በታች ተዘርዝረው ካሉ ድርጅቶች ጋር ጥምረት ፈጥሯል።

1. የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር
2. የደቡብ ህዝቦች ፍትህና እኩልነት ግምባር
3. የቤንሻንጉል ህዝብ የነፃነት ንቅናቄ
4. የትግራይ ህዝብ ዴሞክራስያዊ ንቅናቄ




**"የኢትዮጵያውያን ጥምረት ለዴሞክራስያዊ ለውጥ /ኢጥዴለ/"** በሚል ስያሜ ጥምረት ፈጥሮ ነበር። ጥምረቱን ትህዴን በሊቀመምበርነት ተመርጦ መርቶታል። ይህ ፍፃሜ ጠባብ ናቸው ለትግራይ ብቻ ነው የሚታገሉ እያሉ ስማችን በማጥፋት ላይ ለነበሩ ጠላቶቻችንና ተቃዋሚ ድርጅቶች አፋቸውን ያስዘጋ የተሳካ እርምጃ ነበር።




እነዚህ **"የኢትዮጵያውያን ጥምረት ለዴሞክራስያዊ ለውጥ"** የመሰረቱ አራት ድርጅቶች ሁላቸውንም ያማከለ የጋራ ስምምነት ከመፍጠር አልፈው የጋራ አላማቸውንና እድገታቸውን ለህዝብ የሚገልፁበት፣ የኢህአዴግ ስርዓት በህዝባችን ላይ እየፈፀመው ያለውን ግፍ የሚገልፁበት፣ ህዝብ ወደ ትግል እንዲወጣ የምያነሳሱበት የጋራ ክንድ አስፈላጊነቱን የሚገልፁበት **"ትግል እስከ ድል"** የሚል የጋራ ልሳን የያዘ መፅሄት በማዘጋጀት ወደ ህዝብ እንዲደርስ አድርገዋል።

ይሁን እንጂ ይህ ጥምረት እንደ አጀማመሩ አልቀጠለም ለሦስት ዓመት ያህል ቀዝቅዞ ከቆየ በኋላ ዳግም አወንታዊና አሉታዊ ጎኖችን ተገምግመው ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ/ም ጥምረቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ኢህአግ ከጥምረቱ ራሱን አግልሎ ጋህነን ደግሞ ወደ ጥምረቱ ገብቶ ትህዴን የሚገኝባቸው አራት ድርጅቶች ጥምረቱን አጠናክረው ቀጥለውበታል።

1. የትግራይ ህዝብ ዴሞክራስያዊ ንቅናቄ
2. የኢትዮጵያ ህዝቦች ፍትህና እኩልነት ግምባር

3. የጋምቤላ ህዝብ የነፃነት ቅናቂ
4. የቤንሻንጉል ህዝብ የነፃነት ንቅናቄ



ይህ ጥምረት በፊቱ ከነበረ ጥምረት ለየት የሚያደርገው ከየድረጅቱ የተወሰኑ ታጋዮች እንዲዋጣ በማድረግ እስከ የጋራ የጥምረት ሰራዊት መመስረት ሊደርስ መቻሉ ነው።

ቀጥሎ ደግሞ በ2005 ዓ/ም ጥምረቱ እንዲሰፋ ተደርጓል። የጥምረቱ አባል ድርጅቶች ቁጥራቸው ጨምሮ ከአራት ወደ ሰባት ከፍ እንዲል ተደረገ። የጥምረቱ አባል ድርጅቶች ደግሞ እነዚህ ነበሩ፡-

1. የትግራይ ህዝብ ዴሞክራስያዊ ንቅናቄ /ት.ህ.ዴ.ን/
2. የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግምባር /ኢ.ህ.አ.ግ/
3. የኢትዮጵያ ህዝቦች ፍትህና እኩልነት ግምባር /ኢ.ህ.ፍ.እ.ግ/
4. የቤንሻንጉል ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ /ቤ.ህ.ነ.ን/
5. የጋምቤላ ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ /ጋ.ህ.ነ.ን/
6. የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ /አ.ድ.ሃ.ን/
7. ግንቦት ሰባት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ነበሩ። ይህ ደግሞ በሂደት ሊፈጠር ለሚችለው ውህደት የሚያበረታታ የወደፊት አንድ እርምጃ ነበር።

በውጤቱም ጥምረት ያካሄዱት ሰባት ድርጅቶች መካከል ሁለቱ ማለትም የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄና የኢትዮጵያ ህዝቦች ለፍትህና እኩልነት ግንባር ከአንድ አመት በኋላ በመስከረም 18 ቀን 2006 ዓ.ም ከጥምረት በዘለለ ሙሉ ለሙሉ ውህደት ለመፈፀምና ሰራዊታቸውን ለማቀላቀል የቻሉበት ደረጃ ደርሰዋል።

በ2007 ዓ.ም መጨረሻ ደግሞ አራት ድርጅቶች የሚገኙበት "አገር አድን" የተባለ ጥምረት ተመስርቶ ነበር። የዚህ ጥምረት አባል ድርጅቶች ደግሞ፤

1.የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን)
2.የአርበኞች ግንቦት ሰባት ለፍትህ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ
3.የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ (አድኃን)
4.የአፋር ድርጅቶች የጋራ ንቅናቄ ሲሆኑ ይህ ጥምረት ብዙ ያልተሰራበትና ገና በጅምር ላይ ያለ ነው።

ስለዚህ የትህዴን ድርጅት ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ እንደ አቋም ይዞት የተነሳ በአገር አንድነትና ሉአላዊነት ከሚያምኑ ታጋይ ሃይሎች ጋር አብሮ መስራት፣ ከጥምረት እስከ ውህደት መድረስ በሚል እምነቱ በትልቁ ሰርቶበታል። እንደዚህ በማድረጉም ትህዴን የሚባል ድርጅት ለትግራይ ብቻ የቆመ ጠባብ ብሔራዊ ድርጅት ነው የሚል አስተሳሰብ ይዘው የሚሰብኩ ወገኖች ሐቁን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል።



ዛሬም ድርጅታችን በመሬት ላይ ሊሰራ የሚችል በጋራ ክንድ የሚያምን ድርጅት ስለሆነ በአንዲትና ጥምርት ኢትዮጵያ ከሚያምኑ ድርጅቶች ጋር ይሁን ግለ ሰቦች የህዝባችንንና የአገራችንን ጥቅም በማይነካ መልኩ አብሮ ለመስራት ዝግጁ ነው። ምክንያቱም ጠላታችን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጠላት ስለሆነና ትግሉም “የጋራ ክንድ ለማይቀረው ድል” መሆን አለበት ብሎ ስለሚያምን።

ይሁን እንጂ ድርጅታችን ትህዴን ከተመሰረተችበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ደርሰንበት ያለነው መድረክ እነዚህ ከላይ እየገለፅናቸው የመጣናቸውና ሌሎች ያላነሳናቸው ሰፊ ፖለቲካዊ ተግባሮች በመፈፀም ይህ በህዝብ ለህዝብ እየተካሄደ ላለው የትጥቅ ትግል ለማጠናከር ተንቀሳቅሷል። ዛሪም ይሁን ነገ ትህዴን በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ከሚያምኑ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመስራት ቅርብ ነው።

## ሐቀኛ ሚዲያ!!



የትህዴን የሚዲያ ክፍል ፖለቲካዊ ተግባራቱ ወደ ህዝብ ማሰራጨት ከሚጀምር በሬድዮ በኩል 13 ዓመት፣ በቴሌቪዥን 07 ዓመት፣ በመረጃ ቋት /ኢንተርኔት/ ደግሞ 5 ዓመት አስቆጥሯል። ከዚህ ቀጥለን እነዚህ የተጠቀሱትን አማራጭ ሚዲያዎች ተደማጭነታቸው ምን ይመስል እንደነበር እናስቃኛችው አለን።

የትህዴን የሚዲያ ክፍል የትግሉ አንጎል ወይም የትግሉ ምሰሶ ነው ማለት ይቻላል። እንደዚህ ስለሆነ ደግሞ ከተመሰረተበት ወቅት ጀምሮ እስካሁን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በሰው አቅምና በማቴርያል እንዲያድግ ተደርጓል። እንደውጤቱም ብዛት ያላቸው በስርዓቱ ሳንባ ብቻ የሚተነፍሱ ሞያዊ ስነምግባር የሌላቸው ሚዲያዎች ወያኔ ለሚያሰራጨው የሃሰት ወሬ ገጥመው በመመከትና የድርጅቱን ፖለቲካዊ ንቃትና ጥንካሬ የአላማና የአቋም ግልፅነት ለህዝብ ለማስተዋወቅ ቀዳሚ ነው።


ክፍሊ ሚድያ ዴ.ም.ህ.ት

በህዝባችንና በአገራችን ላይ የሚፈፀሙ ግፎችና በደሎች ወደ አልሰማው ህዝብ ጆሮ እንዲደርስ በማድረግ ስርዓቱ የሸፈናቸውን እውነታዎች ገላልጦ በማውጣት ህዝብ እንዲሰማቸው በማድረግ የትህዴን ሚዲያ ተመራጭ ሚዲያ ሆኖ እየሰራ ቆይቷል። የትግራይ ህዝብ

ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ሬድዮ መጋቢት 21 ቀን 1995 ዓ.ም ከተከፈተ በኋላ በየግማሽ ሰዓት በሳምንት ሁለት ጊዜ፣ በ1998 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በሳምንት ሶስት ጊዜ በግማሽ ሰዓት፣ ከ2002 እስከ አሁን ደግሞ በሳምንት አምስት ጊዜ በየግማሽ ሰዓት እያሰራጬች ቆይታለች።

በነዚህ ዓመታት ደግሞ በፅሁፍ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ልዩ ዝግጅት፣ የጋራ ውይይት፣ ትረካ፣ በረጃጅም የሬድዮ ድራማዎችና ኮሜዲዎች ስኬታማ የሆነ ስራ እንደሰራች የሚመሰክርልን የትህዴንን ሬድዮ ሰምተን መጠናል እያሉ ወደ ትግላችን የሚሰለፉ ታጋዮች በጣም በርካታ ናቸው።

የየካቲት ውለታ ቴሌቪዥን የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም ስርጭት ከምትጀምር እስከ ዛሬ ደግሞ በሬድዮና በቴሌቪዥን ሁለቱ እየተመጋገበ ተወዳዳሪ ሚዲያ ለመሆን በቅቷል ብቻ ሳይሆን፡ ህዝባችን ከሁሉም ሚዲያዎች አብልጦ የእውነተኛ የመረጃ ምንጭ እያለ ይከታተለናል። ምክንያቱም ከስርዓቱ ሚዲያዎች ውጭ ሌላ ስለ አገሩ ሁኔታ የሚሰማበት አማራጭ ሚዲያ ያልነበረው ህዝባችን ሚድያችንን ታላቅ ብስራት ሆኖታል።



ከዚህ በማይለይ ደግሞ የድርጅታችን ድሕረ ገጽ /ዌብ ሳይት/ የዚህ ሚዲያ አካል ነው። www.demhitonline.com በሚል ስያሜ በ2003 ዓ.ም አሃዱ ብሎ የጀመረ የድርጅታችን ድህረ-ገጽ በሬድዮና በቴሌቭዥን የተሰሩ ፕሮግራሞች ወደ መላው ዓለም እንዲደርስ በማድረግ ራሱን የቻለ ድርሻ ነበርው።

የተለያዩ ረጃጅም ፅሁፎችን፣ መግለጫዎች፣ ሐተታዎች፣ ግጥሞች፣ ዕለታዊ ዜናዎችና አጭር ግን ደግሞ አስፈላጊ መልእክት የያዙ ቪዲዮችንም በዌብ በኩል ወደ ተከታታዮቻችን አድርሰናል። ይህ ድህረ ገጽ የተለያዩ ቁም ነገሮችን የያዘ ስለሆነ ሰው ድህረ ገጻችንን ከፍቶ በመረጠው አምድ በመግባት የድርጅታችንና የአገራችንን ሁኔታ ህዝባችን እንዲያውቅ በማድረግ ሰፊ አማራጭ ሆኖ ቆይቷል።

የዚህ ሚዲያ ብልጫ ደግሞ በሬድዮና በቴሌቪዥን የምንለቃቸው ሃቆች የመረረው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በህዝብና በአገር ሃብት ያልተገደበ ወጭዎችን እየከፈለ ዘመናዊ መሳሪያዎችን እየገዛ የየካቲት ውለታን ቴሌቭዥንን ያፍንበት በነበረ ወቅት በዌብ-ሳይት በኩል አድርገን ልንዋጋና ልንመክት ተችሏል።



የት.ህ.ዴ.ን የሚዲያ ክፍል ብዙ አማራጭ መስመሮች ይዞ ነው እየሰራ የቆየው። በላይ እየገለፅናቸው የመጣን አማራጮች ደግሞ የድርጅታችን ልሳን የሆነች ብስራት መፅሄት በ1999 ዓ.ም አሃዱ ብላ የመጀመሪያ እትም ከምትጀምር ከዚህች ከዛሬዋ ጋር ጨምሮ ለ24 እትሞች ተዘርግታለች። በዚህ ደግሞ ታላላቅ ሃሳቦች እያነሳች ለንባብ ስላበቃች በተለያየ መንገድ ወደ ህብረተሰባችን እንድትደርስ በማድረግ ተነባቢ ሆናለች።

በሩቅ አካባቢ ለሚኖር ህዝባችን በድርጅታችን የመረጃ መረብ በኩል አድርገን ወደ ሁሉም ዓለም ስለምንዘረጋው በቅርብ ቤቱ ቁጭ ብሎ እንዲያነባት ሰፊ እድል ፈጥረናል። ስለዚህ የድርጅታችን ልሳን የሆነች ብስራት መጽሄትም እንደ ሬድዮና ቴሌቪዥን ትህዴን ለህዝባችን በማንቃትና በማደራጀት ተግባሮች፣ ስርዓቱን በማጋለጥ የራሷ አበርክቶ እያደረገች መጥታለች።

ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በፓምፕሌት /በራሪ ፅሁፎች/ በኩል የተሰራ ስራም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ መጥቷል። ይህንን ሁሉ ስራ የሚያከናውኑ በርካታ ሞያተኞችን ደግሞ ትህዴን በየጊዜው በውስጣዊ አቅሙ ታጋዮች በታጋዮች እንዲሰለጥኑ በማድረግ ወደ ስራ መድቧል። እንደዚህ ስለተደረገ ደግሞ የትህዴን ሚዲያ ሐቀኛ፣ ታማኝና ተመራጭ ሚዲያ ለመሆን በቅቷል።

## የትህዴን ወታድራዊ ዘመቻዎች

የትጥቅ ትግል ማለት ጦርነት ማለት ነው። ጦርነት ደግሞ ፅናትና መስዋዕትነት የሚጠይቅ መድረክ ነው። ይሁን እንጂ በሰላማዊ መንገድ ሊፈታ የማይችል ችግር በሚገጥምህ ጊዜ ተገደህ የምትወስደው አማራጭ የትጥቅ ትግል ነው። ሩቅ ሳንሄድ የትግራይ ህዝብ የደርግን ስርዓት ለማስወገድ ባነሳው የ17 አመት የትጥቅ ትግል በሺዎች የሚቆጠሩ ህይዎትና የህዝብና የአገር ንብረት እንደወደመ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ይህንን መራራ ጦርነት አካሂዶ በድል ያጠናቀቀ ህዝብ የታገለላቸው አላማዎች በጥቂት ከዳተኛ መሪዎች ተዘርፎ የእጁን አላገኘም። ይሁን እንጂ ህዝባችን በካሃዲዎች መሪዎች ለሚደርስበት በደልና ግፍ አሜን ብሎ ሊቀበልና አቀርቅሮ ሊያነባ አልመረጠም። እንዲያውም ለዚህ ሩቅ ሄዶ ላለው በትህዴን የሚመራ የትጥቅ ትግል ሊያነሳ ተገዷል። እነሆ ላለፉ 15 ዓመታት ለዚህ ፀረ ህዝብና አገር ለሆነ ስርዓት ለማስወገድ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛል።



ከድርጅታችን ምስረታ በኋላ በአንድ አመት ውስጥ በ1994 ዓ.ም የመታገያ አላማውን ለህዝብ ለማስተዋወቅ ያለሙ ሦስት የመጀመሪያ ወታደራዊ ዘመቻዎች ተካሂደዋል። እነሱም በምዕራብ በኩል ሑመራ፣ ጎብለል፣ አደባይ፣ ራውያን አካባቢ እስከ ዳንሻ ነበሩ። በሰሜን ምዕራብ በኩል ደደቢት አካባቢ ዘመቻዎች አድርጓል። በአጠቃላይ ትህዴን ከእነዚህ የመጀመሪያ ወታደራዊ ዘመቻዎች ጀምሮ እስካሁን ያካሄዳቸው ወታደራዊ ተግባራት በጠላት ላይ ያወረደው ጉዳትና የተጎናፀፈው ድል ምን ይመስላል ለሚለው ከዚህ በመቀጠል አንድ ባንድ እናያቸዋለን።

ትህዴን ከአንደኛው ድርጅታዊ ጉባኤ በፊት በነበረ ጊዜ አንዳንድ ወታደራዊ ስራቶች ያካሂድ የነበረ እንኳን ቢሆን በሰፊው አላማውንና ፕሮግራሙን ለህዝብ በማስተዋወቅ ነበር ተጠምዶ የነበረው። ታጋይ በላዩ ላይ ያለውን አደራ ከግቡ ለማድረስ ውስጣዊ አቅሙን በመገምገም ህዝቡን ለማደራጀት በሚችል ስልትና ስትራቴጂ እየተመራ ታላላቅ ወታደራዊ ስራዎች ለማካሄድ ሰፊ እንቅስቃሴ ነው የጀመረው።

ከታሪካዊ አንደኛ ድርጅታዊ ጉባኤ በኋላ የትህዴን ወታደራዊ ኮሚቴ የታጋዩን ብቃት በሚገባ በመገምገም ወታደራዊ ዘመቻ ሊያካሂድ እንደሚችል ስላመነ በጋንታዎች በማቆም ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ትግራይ ባለው ዝርግ መሬት ጥቃት ለመፈፀም የሚያስችሉ ስዕላዊ ጥናትና ስለያዊ ጥናት ሊያሰባስብ ጀመረ።

ይህ ሲጠናቀቅ ቀደም ሲል በትንሽ የሰው ሃይል በማዕከላዊ ዞን ዓባቅ አካባቢ፣ በሰሜናዊ ምዕራብ ዞን ቀላይ ጭየና ዓዲ ፀፀር፣ በምዕራብ ትግራይ ደግሞ በራውያን አካባቢዎች ያካሄደው ወታደራዊ ዘመቻዎች መነሻ በማድረግ በአይነቱ ልዩ የሆነ “ታጠቅ” በተሰኘ ወታደራዊ ዘመቻ ጀምሮ ታጋዩ ሲጠብቀው ለነበረው ወታደራዊ ዘመቻ ጊዜው ደርሶ ተነስ ተብሎ እንደሚያጠቃ ሲነገረው ከመጠን በላይ ሞራል ሰንቆ ነው የተነሳው።



የዚህ ዘመቻ አላማ ስርዓቱ በህዝባችን ላይ ይፈፅመው የነበረውን በደል ለመቀነስ በተለይ ደግሞ በጊዜው አደገኛ ቦዘኔ በሚል ስም ተሰጥቶት ሲንገላታ የነበረው ወጣት ለማዳን፣ እንዲሁም ሳይወድ በሰፈራ ስም ወደ ሀሩር በረሃዎች በማስፈር ለመራራ ህይወት የተፈረደበትን ህዝባችንን ለማላቀቅ፣ በትልቁ ደግሞ በወያኔ የተካደውን የህዝባችንን ጥያቄ ለመመለስና ህዝባችን ዋስና ጥላ የምትሆነው ትህዴን እንዳለችው ለማብሰርና ህዝብ ካለበት ስቃይና ችግር እንዲዎጣ አማራጮቹን ራሱ እንዲወስን ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከድርጅቱ ትህዴን ጋር እንዲሰለፍ ለማድረግ ያለመ ነበር።

ይህንን አላማ አንግቦ የተነሳ ታጋይ ደግሞ ድንገተኛ ጥቃቱን በስተምዕራብ አቅጣጫ አሃዱ ብሎ በመጀመር ጥር 11 ቀን 1998 ዓ.ም ወደ በረከት ከተማ ዘልቆ በመግባት በቦታው የነበረውን ክምቹ ሰራዊት በመደምሰስ የድርጅቱን አላማ ሲያስረዳ፡ ረመጥ ያዘለው ሁለተኛው አሃዱም ልጅ በተባለ አካባቢ የነበረ የጠላት ሃይል ድንገተኛ ጥቃት በመክፈት የቦታው አዛዦች የሚገኙበት የወያኔ ወታደሮች አርበትብቶ በመቅጣት የመጀመሪያ ግቡን አጠናቋል። በዚህ ዘመቻ ታጋያችን በላዩ ላይ ከመጠን በላይ የጠላት ቦምብና ጥይት የወረደበት ቢሆንም በፅናትና በብልሃተኝነቱ በማለፍ የጠላትን ካምፖችንና ትጥቁን በማቃጠል ወታደራዊ ኃይሉን በተግባር አስመስክሯል።



በሌላ በኩል ለማይካድራ ከተማ በሰሜናዊ ምዕራብ በኩል አንድ ሃይል፣ የበረከት ከተማን ለሁለተኛ ጊዜ ሌላ ሃይል በራውያን አካባቢ በነበረ የጠላት ሰራዊት በተመሳሳይ ሰዓት ጥቃቶች ተተግብረዋል። የጠላት ግብረ መልስ ደካማ ስለነበር ሰራዊታችን የሚደመሰሰውን ደምስሶ የጠላትን ካምፕ ከተቆጣጠረ በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ የጠላት ወታደሮች ከስራ ውጭ ከማድረጉም በላይ ሁለት ቶዮታ አይነት መኪኖችን ጨምሮ በርካታ

የጠላት ንብረት አውድሞ ድርብ ድል አስመዝግቧል። በዚህ ስሪት ደግሞ ተነግረው የማያልቁ ድንቅ ታሪኮች ተፈፅመዋል።

በምዕራብ ዞን ታሪክ የሰራ ታጋይ አቅጣጫውን ወደ ሰሜናዊ ምዕራብ በማዞር ወታደራዊ ማጥቃቱን አጠናክሮ ቀጥሎበታል። በዚህ መሰረት ደግሞ በላዕላይ አድያቦ ወረዳ ደጉዓለ በተባለ ቦታ የነበረውን የጠላት ወታደር አምበርክኮ በመቅጣት ህዝብን ይበድሉ በነበሩ ካድሬዎችና የሚልሻ አባላት አስተማሪ እርምጃ ከወሰደ በኋላ፡ ትጥቅና ዘመናዊ የመገናኛ ሬድዮኖችን ለመማረክ ችሏል። ጠላት ደግሞ በምዕራብ ዞን ባጋጠመው ከባድ ሽንፈት ተደናግጠና ተንቀጥቅጦ ስለነበር በዱጋለ ጥቃት መሽጎ ከመዋጋት ይልቅ እግሬ አውጭኝ ሲፈረጥጥ ታይቷል።

ታጋይ እነዚህ ሲመዘገቡ የቆዩ ወታደራዊ ድሎች አቅቦ ሳይኩራራ ወደ ሰሜናዊ ምዕራብ በመገስገስ በኬላ ዕጉብና ዓዲ ርእሶ አካባቢ በነበረ የወያኔ ማሌሊት ሰራዊት ላይ ጥቃቶቹን በመለኮስ በመቶዎች የሚቆጠሩ የወያኔ ሰራዊት ከስራ ውጭ በማድረግ ተልዕኮውን ሲፈፅም፡ ለትህዴን ትግል ወቅታዊነት በገሃድ በማረጋገጥ ለበለጠ ወታደራዊ ስራዎች ከጊዜ ጋር ቅድድም የገጠመበት ወቅት ነበር።



የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ተላላኪ ሰራዊት በነፍስ ወከፍ ዘመቻዎቻችን የአልሞትኩም አለሁ ተደጋጋሚ ደፈጣዎችን እንኳ ቢፈትንም የመሳሪያ ብዛት ሳይሆን ትክክለኛ መስመር ስለሚያሸንፍ የህዝብና የአገር አላማ አንግቦ የሚሽቀዳደመው የትህዴን ታጋይ ለማሸነፍ በቅቷል።

በእጉብ የተካሄደ ወታደራዊ ዘመቻ ብዙ መሰናክሎች የነበረው በርከት ያሉ ደፈጣዎች የታለፉበት፣ ከበድ ያለ ወታደራዊ ማጥቃት ነው የነበረው። የትህዴን ታጋይ ግን የህዝብና የአገር አላማን ተሸክሞ የተነሳ ስለሆነ፡ በሚገጥሙት ፈተናዎች ሲበረታ እንጂ ሲንበረከክ አልታየም።

በጠቅላላ የታጠቅ ዘመቻ በርከት ያሉ የጠላት ሰራዊት የሞቱበትና የቆሰሉበት፣ ከአስር በላይ ጠላት ሲገለገልባቸው የነበሩ መኪኖች የተቃጠሉበት፣ ኃይለኛ ከባድና ቀላል የጠላት መሳሪያዎች የተማረኩበት፣ ሦስት ፒአርሲ ዓይነት የመገናኛ ሬድዮች በመማረክ ወታደራዊ ስሪታችን ከፍ ወዳለ ደረጃ የተሸጋገረበት መድረክ ነበር። የታጠቅ ዘመቻ ከጫፍ እስከ ጫፍ የጠላታችንን ሞራል የሰበረ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የትህዴን ታጋይ ብቃት የተረጋገጠበት ህዝባችን የልቡን ያገኘበት፣ ውጤታማ ህዝባዊ ተልእኮዎች የተከናወኑበት የለውጥ መድረክ ያካተተ ዘመቻ ነበር።

በ1998 ዓ.ም የነበሩ ጠንካራ ጎኖቹን በማስቀጠል ለበለጠ ዘመቻው እቅዶቹን ሲያዋድድ የቆየ የትህዴን ወታደራዊ ኮሚቴ በ1999 ዓ.ም "**ውፊር ተበገስ**" የተሰየመ ወታደራዊ ዘመቻዎቹን በተጠናከረ መልኩ ነው የቀጠለበት። በዚህ መሠረት በሕዳር ወር 1999 ዓ.ም በትግራይ ማዕከላዊ ዞን በምኹዓት ሳዳና ምዳቅ ምፃይ አካባቢ በነበረ የሰሜን እዝ አግአዚ በተባለ ክፍል ጦር ሰራዊት ላይ ድንገተኛ ጥቃት በመክፈት በርካታ የጠላት ሰራዊት ከስራ ውጭ ሲያደርግ በርከት ያሉ ትጥቆችንና ተተኳሾችን አውድሞና ማርኳል።



ይህ በአግአዚ ክፍለ ሰራዊት ላይ የተወሰደው ጥቃት ከፊት ከነበሩት ጥቃቶች ልዩነት አልነበረውም። የሚለየው ነገር ካለ አሃዱው ከተለያዩ ክፍሎች ባላቸው አቅምና ለስርዓቱ ባላቸው ታማኝነት ተመልምለው የተሰበሰቡ መሆናቸው ብቻ ነው። በተግባር ስንመዝነው ግን ከሌሎች ጥቃት ካካሄድንላቸው አሃዱዎች የተሻለ አቅም አልነበረውም። በሌላ በኩል በህዳር ወር 1999 ዓ.ም በትግራይ ማዕከላዊ ዞን መረብ ለከ ወረዳ፡ ዓዲ ጋባትና ክሳድ ሐንሰ አካባቢዎች በነበረ የሰሜን እዝ ክፍለ ሰራዊት 14ኛ ተዋጊ አሃዱ፣ በመቀጠለም በታህሳስ ወር 1999 ዓ.ም በማዕከላዊ ዞን መረብ ለከ ወረዳ ክሳድ ሳህዳድና ዓባቕ አካባቢዎች በነበረ የወያኔ ሰራዊት የመረጃ አሃዱ ላይ በወሰደው ጥቃት የሃምሳ አለቃ አዛዥ የሚገኝባቸው በርካታ ወታደሮች ከስራ ውጭ አድርጓል።

በታህሳስ 23 ቀን 1999 ዓ.ም በመረብ ለከ ወረዳ መንደር አንደ ወርቅና ጠራውር በነበረ የ14ኛ ክፍለ ሰራዊት አራተኛ ሬጅመንት በወሰደው የማጥቃት እርምጃ በርከት ያሉ የጠላት ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ ከዚህ በላይ በርከት ያሉ ክላሽ ኮፍና የእጅ ቦምቦችና ሌሎች ወታደራዊ የጦር መሳሪያዎችን ማርኳል። የትህዴን ድርጅት በ1999 ዓ.ም በጠላት ላይ የወሰዳቸው ወታደራዊ ማጥቃቶችና ስራቶች በጣም በርከት ያሉ ከመሆናቸውም በላይ የየራሳቸው ብልጫዎች ለየት የሚያደርጋቸው ነጥቦችም ነበሯቸው።

ታህሳስ 25 1999 ዓ.ም ሁለት አሃዱ በጋራ በመሆን በሽራሮ ወረዳ ሰምሓል ቀበሌ በአዲ አድሃናንና ሃይቀዳማ በሶስት የጠላት ካምፖች የተሰነዘረ ስኬታማ ወታደራዊ ስራት ነበር። በዚህ ዘመቻ በርከት ያሉ የጠላት ወታደሮች ከስራ ውጭ ሲሆኑ ሁለት ቲም አመራሮች የሚገኙበት ወታደሮች ተማርከዋል። ሶስት አይኮም ዓይነት የመገናኛ ሬድዮና በርካታ የጦር መሳሪያዎችንም ተማርከዋል።

ጥር 2 ቀን 1999 ዓ.ም በላዕላይ አድያቦ ወረዳ ደጉዓለና ማይ ሰስሐ አካባቢ በነበረ ከአንድ ሻምበል በላይ የሚሆን የ29ኛ ክፍለ ሰራዊት በወሰደው ወታደራዊ ዘመቻ ታጋያችን በርከት ያሉ ወታደሮችን ከስራ ውጭ በማድረግ ጠላት ሲገለገልባቸው የነበረ የህክምና መስጫ መሳሪያዎችና ትጥቆችን ማርኳል።

ጥር 11 እና 12 ቀን 1999 ዓ.ም በላዕላይ አድያቦ ወረዳ ዕልምና ዕዳጋ ባርያ፣ ዓዲ አባርእሶ፣ ዓዲ ጎልጎልና እንዳ አምሓራይ ላይ በነበረ የ29ኛ ክፍለ ሰራዊት የመረጃ አሃዱ ላይ በወሰደው ጥቃት በርከት ያሉ የጠላት ወታደሮች በመግደልና በማቁሰል የድርጅቱን አላማ የሚገልፁ የትግል ዘፈኖችንና በራሪ ፅሁፎችን እንዲሁም ብስራት መፅሄትን ለህዝቡ አድሏል።

ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም በመረብ ለከ ወረዳ ዓዲ ሽምብሩህ ቀበሌ መንደር ዓዲ እቁባላሰ ላይ በነበረ የ14ኛ ክፍለ ሰራዊት አንድ ሻንበል፣ ከ33ኛ አግአዚ ክፍለ ሰራዊትና የተወጣጣች አንድ የሰሜን እዝ የመረጃ አሃዱ በወሰደው ነጎድጓዳማ ጥቃት በርከት ያሉ የጠላት ወታደሮችን ሟችና ቁስለኛ በማድረግ ወታደራዊ የጦር መሳሪያዎችን ሲማርክ፡ በካምፑ የነበረውን ሎጀስቲካዊ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ አውድሟል።



ሌላው በአይነቱና በአጨራረሱ አተረጓጎም ልዩ የሆነ ወታደራዊ ዘመቻ ደግሞ በየካቲት ወር 1999 ዓ.ም በአዲ ጎሹ ከተማ የተካሄደው ጥቃት ሲሆን ዘመቻው "የህብረት ዘመቻ ለዴሞክራሲ " በሚል የተሰየመና በትህዴን ድርጅትና የደቡብ ኢ.ትዮጵያ ህዝቦች ድርጅት ታጋዮች በህብረት የተካሄደ ጥቃት ነበር። ይህ ደግሞ ድርጅታችን ትህዴን ለጋራ አላማ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመስራት ያለውን ቅርብነትና ተነሳሽነት የሚያመላክት ወታደራዊ ስራት ነው።

የጠላት ሰራዊት በእነዚህ ስኬታማ ወታደራዊ ዘመቻዎች ላጋጠመው ሽንፈትና እፍረት ለመሸፈን ሚልሻና መደበኛ ሰራዊት አሰባስቦ ፅምብዓ በተባለ ቦታ፣ በክሳድ ፀለቤዱና ዕንጓይላ የደፈጣ ፈተና ቢያደርግም ጀግናው ሰራዊታችን በቦታው አስቀድሞ አድፍጦ በመቆየት ተንደርድሮ እየመጣ በነበረ የጠላት ሰራዊት አጋጭቶ በመመለስ ሽንፈትን ስያከናንበው፡ ከዚህም በላይ የአካባቢው አስተዳዳሪ የሚገኙበት ፀረ ህዝብ ሚልሻዎች የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ለሌሎች በርከት ያሉትን ደግሞ ማርኮ የድርጅቱን አላማ አስረድቶ ለቋቸዋል።

ታጋዩ ከወታደራዊ ዘመቻው ጎን ለጎን የትግሉን ዋነኛ መነሻ የሚገልፁ የድርጅታችን ልሳን የሆነችውን ብስራት መፅሄት፣ የትግል ዘፈኖች የያዘ ካሴትና ሌሎች በራሪ ፅሁፎችን ለህዝብ አድሏል። የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ወያኔ ለሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ባለመስማቱ ሰላም ካልተረዳው በትጥቅ ትግል መወገድ አለበት ብሎ ያምናል። ከመጀመሪያ ምስረታው ጀምሮ ደግሞ በህዝብ ከፍተኛ ተቀባይነትና ወቅታዊ አማራጭ የትጥቅ ትግሉን ብዙ ተከታዮችን አግኝቶ ከጊዜ ወደ ጊዜ አደረጃጀቱንና አቅሙን አደላድሎ ከጠላቱ ጋር ፊት ለፊት ገጥሞ ሃያልነቱን ሊያረጋግጥ ችሏል።

ጠላቶቻችን በላያቸው ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳለን ብቻ ሳይሆን በድርጅታዊ እምነት ያለን የማይነቃነቅ ፅኑ የሆነ ሃይል እንደማይለውጠው ጥሩ አድርገው ያውቃሉ። ትህዴን በ1998 ዓ.ም እንዲሁም በ1999 ዓ.ም የተጎናፀፋቸው አበራታች ድሎች አስጠብቆ ለ2000 ዓ.ም በድል ነው የተቀበለው።

በ2000 ዓ.ም ደግሞ **"ፈዳይ"** በሚል የዘመቻ ስያሜ ወታደራዊ ዘመቻውን ቀጥሎበታል፡ በዚህ መሰረት ታጋያችን ጥር 28 ቀን 2000 ዓ.ም በማዕከላዊ ዞን ዕዳጋ ቀዳም በተባለ ቦታ በወሰደው ድንገተኛ ጥቃት በአስራዎች የሚቆጠሩ የጠላት ወታደሮችን ከስራ ውጭ ያደረገ ሆኖ በሌላ በኩል ደግሞ የትህዴን ልዩ ሃይል በመረብ ለከ ወረዳ ደብረ ሃርማዝ ቀበሌ መንደር ሻኩትና በማይ ሁመርና አካባቢዋ በጥበቃ ተሰማርተው በነበሩ የወያኔ ወታደሮች ላይ ድንገተኛ ማጥቃት በመሰንዘር ድሎችን ተጎናፅፏል።

በጥር መጨረሻ 2000 ዓ.ም በዕዳጋ ቀዳም በተካሄደ ውጊያ የድርጅታችን ሊቀመንበር የነበረ ጓድ ፍስሃ ኃይለማርያም በተሰዋበት ሰሞን የተፈፀመ ሆኖ፡ በወቅቱ ጠላት ከእንግዲህ ምንም አይሰሩም ሊቀመንበራቸው ተሰውቷል፣ ተስፋ ይላቸውም፣ ሊፈርሱ ነው በሚል ፕሮፖጋንዳ ተጠምዶ የነበረበት ወቅት በመሆኑ የተገኘው ድል ህላዌያችንን ከማረጋገጥ

አልፎ ደልዳላ ወታደራዊ መሠረታችን የሚያረጋግጥና ሁለት ትርጉም ያለው ታላቅ ድል ነው።




የካቲት 6 ቀን 2000 ዓ.ም ደግሞ በሰሜናዊ ምዕራብ ትግራይ ዞን ታህታይ አድያቦ ወረዳ በነበረ የ33ኛ ክፍለ ሰራዊት የመረጃ ሻንበል፡ በተመሳሳይ በተወሰደ ስራት የጠላት ሰራዊት ያለ ወሬ አድራሽ ተርፏል። የጠላት ሰራዊት ውኃ ይቀዳበት የነበረ የውሃ ጋን እንዲወድም ተደርጓል።

የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሰሜናዊ ምዕራብ ዞን ላዕላይ አድያቦ ወረዳ ዕጉብ ቀበሌ መንደር ምድረ ፈላሲ ሰፍሮ በነበረ የ24ኛ ክፍለ ሰራዊት 6ኛ ሬጅመንት ላይ በወሰደው ጥቃት በርከት ያሉ የጠላት ወታደሮች ሲገደሉ፡ ነሐሴ 20 ቀን 2000 ዓ.ም በሰሜናዊ ምዕራብ ዞን ላዕላይ አድያቦ ምድረ ፈላሲ ቀበሌ መንደር ዓዲ ሓመዶ በተካሄደ ደፈጣ በ24ኛ ክፍለ ሰራዊት 2ኛ ሬጅመንት የመረጃ አሃዱ ላይ የወሰደው ጥቃት ብዙ የስርዓቱ ወታደሮችን ከስራ ውጭ አድርጓል።



በ2000 ዓ.ም የተነሳው **"ዘመቻ ፈዳይ"** እነዚህ እና ሌሎች የመሰሉ ወታደራዊ ዘመቻዎች አስተናግዶ ትህዴን ድርጅት ከዚህ ዘመቻ ታላላቅ ድሎችን ተጎናፅፏል። የትህዴን ታጋይ በ2000 ዓ.ም ያገኛቸውን ድሎች አስጠብቆና ብዙ ተሞክሮዎችን ተምሮ ለ2001 ዓ.ም ደግሞ **"ቃል በተግባር"** በሚል ስያሜ ዘመቻ ለማካየድ በደስታ ነው የተቀበለው።

በመስከረም ወር 2001 ዓ.ም በማዕከላዊ ዞን በአድዋ እዳጋ ቀዳም በተባለ ቦታ በነበሩ የስርዓቱ ተላላኪ የፖሊስ አባላትና የፀጥታ አባላት በወሰደው ጥቃት ታላላቅ ድሎችን በማፈስ በድል ከፍቷታል። በመቀጠል በጥቅምት 5- 2001 ዓ.ም በማዕከላዊ ዞን አህፈሮም ወረዳ ሆያ ቀበሌ መንደር መባርዲ በነበረ 20ኛ ክፍለ ሰራዊት ሃንደሳ አሃዱ ላይ በወሰደው ጥቃት በርከት ያሉ ወታደሮች ከስራ ውጭ አድርጓል።

ጥር 5 ቀን 2001 ዓ.ም በምዕራብ ዞን ቃፍታ ሑመራ ወረዳ ዓዲ ጎሹ ከተማና አካባቢው በብርሳሳና ስርባ ዶብ ሰፍሮ በነበረ የ23ኛ ክፍለ ሰራዊት 3ኛ ሬጅመንት ሶስት ሻንበልና አንድ የሃደሳ ጋንታ በወሰደው ድንገተኛ ጥቃት በመቶዎች የሚቆጠሩ የወያኔ ወታደሮች ከስራ ውጭ ሲያደርግ፡ ሃምሳ አለቃ የሚገኝባቸው ብዙ ወታደሮች ደግሞ ማርኳል። እንዲሁም የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች፣ ተተኳሽ ትጥቆችን፣ የመገናኛ ሬድዮችንና ሌሎች የጠላት ዶክመንቶችን ማርኳል።

ከዚህ ሌላ በተመሳሳይ ቀን ማለትም ጥር 5 ቀን 2001 ዓ.ም በምስራቅ ዞን ኢሮብ ወረዳ ዓይጋ አካባቢ ልዩ ስሙ ኩማ ዛግራ በተባለ ቦታ በነበረ የ11ኛ ክፍለ ሰራዊት 3ኛ ሬጅመንት 4ኛ ሻንበል ላይ በወሰደው ድንገተኛ ማጥቃት በአስራዎች የሚቆጠሩ የጠላት

ወታደሮችን ከስራ ውጭ በማድረግ አንድ አስር አለቃ የሚገኙባቸው በርካታ ወታደሮች ማርኮ በርከት ያሉ የጦር መሳሪያዎችንና የጠላት ዶክመንቶችን ተማርኳል።

በተመሳሳይ ዕለት ደግሞ ሌላ የትህዴን አሃዱ ወደ ትግራይ ማእከላዊ ዞን መረብ ለከ ወረዳ ጣብያ ዓዲ በርበረ በማቅናት በቦታው መሽጎ በነበረ የ14ኛ ክፍለ ሰራዊት 2ኛ ሬጅመንት 3ኛ ሻንበል በሰነዘረው ማጥቃት በአስራዎች የሚቆጠሩ የጥላት ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ የተለያዩ ወታደራዊ መሳርያዎች ማርኳል።

የትህዴን ታጋይ የጀመረውን የማጥቃት ዘመቻ በማስቀጠል በሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ/ም በሰሜናዊ ምዕራብ ዞን ታሕታይ አድያቦ ወረዳ ሰምሃል ቀበሌ መንደር ምሕፃብ ዓላቡ በነበረ የ35ኛ ክፍለ-ሰራዊት 2ኛ ሬጅመንት የመረጃና ሃንደሳ አሃዱ በወሰደው ድንገተኛ ስሪት በርከት ያሉ የጠላት ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ ጥላት ሲጠቀምባቸው የነበረ የትጥቅና ስንቅ መጋዘን ሙሉ በሙሉ በማቃጠል አውድሟል።

ትህዴት ከዓመት ወደ ዓመት ሲሸጋገር ልዩ አደረጃጀትና ስያሜ ፈጥሮ ተሞክሮዎችን አካብቶ ነው በሚቀበለው አዲስ ዓመት ካለፈው አሮጌ አመት እጥፍ እንዲሰራ ቃሉን አሳድሶ ነው የሚጀምረው። በዚህ መሰረት በ2002 ዓ/ም ለተካየደው ዘመቻም **"ዘመቻ ትግል ለለውጥ"** በሚል ስያሜ አጅቦታል።

በዚህ መሰረት ሰራዊታችን በጥር 23 ቀን 2002 ዓ/ም በትግራይ ሰሜን ምዕራብ ታሕታይ አድያቦ ወረዳ ዓዲ ፀፀር ቀበሌ መንደር ዓዲ ተኳሉ ልዩ ስሙ ዒላ ሰፍአ በተባለ ቦታ በነበረ የ33ኛ ክፍለ-ሰራዊት 1ኛ ሬጅመንት 2ኛ የሃንደሳና የመረጃ ጋንታ በወሰደው እርምጃ ብዙ ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ ባካባቢው የነበሩ ወታደሮች ሲጠቀሙበት የነበሩ ትልቅ የዋሃ ጀነሬተርና ሁለት የዋሃ መጠራቀምያ ጋን ሙሉ ለሙሉ በማውደም የተለያዩ ወታደራዊ ንብረቶችን ማርኳል።



በየካቲት 10 ቀን 2002 ዓ/ም በትግራይ ሰሜን ምዕራብ ዞን ላዕላይ አድያቦ ወረዳ በዕጉብ መስመር፣ መደባይ ታብር፣ ዓዲ መቁጥንን ሆኖ የትህዴንን እንቅስቃሴ ለማገትና፡ የየካቲት 11 ቀን በዓል ለመጠበቅ ተሰምርቶ በነበረ የ31ኛ ክፍለ-ሰራዊት የመረጃ አሃዱ በተደረገ የደፈጣ ጥቃት በአስራዎች የሚቆጠሩ የጠላት ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ የተለያዩ አይነት መሳርያዎች፣ ተተኳሽ የእጅ ቦምቦችና ሌሎች ወታደራዊ ቁሳቁሶች ማርኳል።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ወያኔ ለዓዲ ርእሶ ቀበሌና አካባቢው ነዋሪዎች ሰብስበው ለየካቲት 11 በዓል ማክበርያ የሚሆን ገንዘብ እንዲከፍሉና ለ2002 ምርጫ የመጨረሻ ካርድ ውሰዱ እያሉ እያስፈራሩት በነበሩበት ወቅት ጀግናው ታጋያችን ድንገት በከበባ በማስገባት ፀረ ህዝብ ለሆኑ ካድሬዎች የሚገባ ቅጣት በመስጠት ተሰብስበው ለነበረው ህዝብ ደግሞ እያካየድነው ስላለን ትግል ትምህርትና መረጃ በመስጠት፣ በመደባይ ታብር ጣብያ ዕጉብ ዓዲ መቕጡንና ዓዲ ርእሶ ለሚኖር ህዝባችን የትግላችንን አላማና ጭቆናችን የሚገልፅ ብስራት መፅሄት፣ በራሪ ፅሁፎችና የትግል ዘፈኖች የያዘ ካሴት አድሏል።

በተመሳሳይ በየካቲት 18 ቀን 2002 ዓ/ም በምስራቅ ትግራይ ዞን ኢሮብ ወረዳ ጣብያ እንዳልጌዳ ቀበሌ ማይ ጨዓ መሸጎ በነበረው የ21ኛ ክፍለ-ሰራዊት 5ኛ ሬጅመንት የመረጃ አሃዱ ላይ በወሰደው ጥቃት ከአስር በላይ የሚሆኑ የወያኔ ወታደሮች ከስራ ውጭ አድርጓል።

በሃምሌ 4 ቀን 2002 ዓ/ም በትግራይ ማእከላዊ ዞን አሕፈሮም ወረዳ ጣብያ ማይ ሓማቶ ቀበሌ ከለሊዕ፡ በነበረው የወያኔ ኢህአዴግ ሰራዊት ላይ በወሰደው ድንገተኛ እርምጃ በአስራዎች የሚቆጠሩ የስርአቱ ወታደሮች ከስራ ውጭ ሲያደርግ፡ በነሃሴ 24 ቀን 2002 ዓ/ም ደግሞ በትግራይ ማእከላዊ ዞን አሕፈሮም ወረዳ፡ ሰምሃል ቀበሌ እንዳርጋብና ገርዓ በነበረ የጠላት ሰራዊት ላይ በሰነዘረው የማጥቃት እርምጃ፡ በሞቶዎች የሚቆጠሩ የስርዓቱ ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ፡ በሰምሃል ቀበሌ ምክትል የምልሻ አዛዥን በቁጥጥር ስር አውሎታል።

በ2002 ዓ/ም ሰፋፊ ድሎችን ያገኘንበት **"ዘመቻ ትግል ለለውጥ"** ከተገባደደ ደግሞ ለ2003 ዓ/ም **"ዘመቻ የካቲት"** በሚል ስያሜ ነው የተቀበለው፡ በጠላት ሰራዊት ላይ ደግሞ አንፀባራቂ ድሎችን ልናገኝበት ችለናል። በዚ መሰረት ደግሞ፡-



ጀግናው ሰራዊታችን የ2003 ዓ/ም ወታደራዊ ዘመቻውን አንድ ብሎ በመጀመር በህዳር 7 ቀን 2003 ዓ/ም በትግራይ ሰሜን ምዕራብ ዞን ዓዲ ዳዕሮ ወረዳ ዕጉብ ቀበሌ መንደር ዓዲ ጎልጎል በ31ኛ ክፍለ-ሰራዊት 4ኛ ሬጅመንት የመረጃ አሃዱ በወሰደው ድንገተኛ ጥቃት፡ በአስራዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች ከስራ ውጭ አድርጓል። ቀጥሎም በህዳር 9 ቀን 2003 ዓ/ም በትግራይ ማእከላዊ ዞን መረብ ለከ ወረዳ ጣብያ ዓዲ ሽምብሩህ ቀበሌ ዓዲ ዑቅባላሰ በነበረው የ14ኛ ክፍለ-ሰራዊት 3ኛ ሬጅመንትና፡ የምልሻዎች ስብስብ ላይ በሰነዘረው ጥቃት በርከት ያሉ የጠላት ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ ሌሎች ሦስት ሚልሻዎችና የተለያዩ ወታደራዊ ንብረቶችን ማርኳል።

ይህ እንዳለ ሆኖ የትህዴን ልዩ አሃዱ በህዳር 9 ቀን 2003 ዓ/ም በሰሜናዊ ምዕራብ ዞን ላዕላይ አድያቦ ወረዳ፡ ምድረ ፈላሲ ቀበሌ በነበረ የ31ኛ ክፍለ-ሰራዊት 4ኛ ሬጅመንት ቴሌቪዥን በሚከታተሉበት አዳራሽ በጠመደው ፈንጅ በርከት ያሉ ወታደሮች ከስራ ውጭ በማድረግ፡ ቤታቸውና ሌሎች ወታደራዊ ንብረቶች ሲያወድም፡ በተመሳሳይ ህዳር 22 ቀን 2003 ዓ/ም የትህዴን ስሪት አሃዱ በምብራቅ ዞን ኢሮብ ወረዳ፡ በዓይጋና ኩማዛግራ መካከል በሚገኝ የወያኔ ወታደራዊ ካምፕ በጠመደው ተተኳሽ ፈንጅ ብዙ ወታደሮች ከስራ ውጭ አድርጓል።

ድርጅታችን ትህዴን በጠላት ላይ ሲወስዳቸው የነበረ፡ የህዝባችን አለኝታ የሆኑ በርካታ ወታደራዊ ጥቃቶች አጠናክሮ በመቀጠል፡ ታህሳስ 13 ቀን 2003 ዓ/ም በትግራይ ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን ሃይቀዳማ በተባለው ልዩ ቦታ፡ በ1999 ዓ/ም ህዳር 25 ቀን ጥቃት ፈፅሞበት የነበረ ካምፕ በድጋሜ በማጥቃት አኩሪ ድል ተጎናፅፏል።




ትህዴን በ1998 ዓ/ም በአፍገበል አንድ ብሎ የጀመረው ወታደራዊ ጥቃት፡ በ2003 ዓ/ም መጨረሻ አቅጣጫውን ወደ ምስራቅ በማዞር፡ በአፋር መሬት አካባቢ ራንዳ ኩማ በተባለ ቦታ መሽጎ በነበረው የጠላት ሃይል በፈፀመው ጥቃት ነው ያኔ ወታደራዊ ዘመቻዎች በድል ያጠናቀቀ።

ይህ ውግያም እንደነ አዲ-ጎሹ በጠራራ ፀሃይ ከጠላት ጋር እየኝ ልይህ፡ ግጠመኝ ልግጠምህ፡ ፊት ለፊት ስለ ነበረ፡ ለትህዴን በወሬ ብቻ ሰምተው በእንቅልፋቸው ሲባንኑ የነበሩ የጠላት ወታደሮች፡ ታጋያችን በጠራራ ፀሃይ መጣሁባቹሁ ሲላቸው፡ አድፍጠው መዋጋት አልቻሉም፡ እግሬ አውጭኝ በገጠማቸው መንገድ ተበታትነው ነው የሸሹ። ታጋያችን ግን የገቡበት ገብቶ አይቀጡ ቅጣት ቀጥቷቸዋል። ቀጥሎ ካምፑ ሙሉ ለሙሉ በመቆጣጠር የሚቃጠል አቃጥሎ፡ አስፈላጊ የሆኑ የጥላት ዶክመንቶችና ወታደራዊ አጽዋር ማርኮ ለራሱ ጥቅም አውሎታል። በዚህ ስራት የቦታው አዛዥ የነበረ ሻምበልና አንድ አስራለቃ በህይወት ተማርከዋል።




አጠቃለን ስናየው ደግሞ ድርጅታችን ትህዴን፡ ከ1998 ዓ/ም መደበኛ የሆነ ወታደራዊ ዘመቻ ማካሄድ ከሚጀምር እስከ 2003 ዓ/ም በጠላት ላይ ከባድ ኪሳራዎችና ውድመት ያደረሱ፡ ለስርአቱ ወታደራዊ አዛዦች በከባድ ስጋትና ፈተና ያስገቡ፡ በርከት ያሉ ወታደራዊ ጥቃቶች ፈፅመዋል።

ከ2003 እስከ ዛሬ ደግሞ ድርጅታችን ያለፉትን ወታደራዊ ዘመቻዎች የነበራቸውን አወንታዊና አሉታዊ ጎኖች በመገምገም፡ አሉታዊ የሆኑ ተግዳሮችን ለማስወገድ የሚያስችሉት ሰፋፊና ተከታታይ ወታደራዊ ስልጠናዎች በማካሄድ ላይ የቆየ ሆኖ፡ አሁንም ህዝባችን ከገባበት ጭቆናና አፈና ለማላቀቅ፡ በአገራችን ፍትሃዊ ስርዓት ለማምጣት የጀመረውን ትግል ከግቡ ለማድረስ፡ በወያኔ ስርአት ላይ የጀመረው ወታደራዊ ማጥቃት ከማንኛውም ግዜ በላይ አጠናክሮ ለማስቀጠል በጥሩ ዝግጅት ላይ ይገኛል።



## የሥኬት ጎዳና

ለብሩህ መፃኢ ችቦ የለኮሰ
የስኬትን መስመር ፕላን የቀየሰ
የህዝብ ህልውና የለውጥ ባለቅኔ
የአንድነት ምሰሶ የእድገት ስልጣኔ
የእኩልነት መድረክ የህዝበ ውሳኔ
አንደበተ ርቱዕ ኢትዮጵያዊ ወኔ፡

አሻግሮ ተመልካች የድልን አቅጣጫ
የብዙሃኖች ድምፅ የፍትሃዊ ምርጫ
በነፃነት መድረክ ሃሳብን መግለጫ
የዴሞክራሲን ቁልፍ በራፏን መክፈቻ፣
መሰረተ ጽኑ ለአገራዊ ራዕይ
የጭቁኖች ተስፋ ጠበቃ ገላጋይ
የድልን ጎዳና መንገዷን አስተዋይ፣
በትግሉ የሰላ ካለፈው ተምሮ
የጠላትን ሴራ ተንኮሉን መርምሮ



በታጋዮቹ ዘንድ ግንዛቤን ፈጥሮ
መቻቻል መዋደድ ህብረት አስተምሮ፣
ለትግሉ ተልዕኮ ውሳኔ የሰጠ
ለተግዳሮቶቹ መፍትሄ ያስቀመጠ
የጨለማን ዘመን ብርሃን የለወጠ
በታሪክ መዝገብ ላይ ፊርማ ያስቀመጠ፣
መመሪያ ደንቦችን ህጎችን አርቃቂ
አደረጃጀቱ በተግባር አመርቂ
ለህዝባዊ ትግሉ ፅናት አስታጣቂ፣
ስለጭቁን ህዝቦች ደሙን የገበረ
በመድረክ ተስሎ ጀግናን የፈጠረ

በወታደራዊ ክንዱ የበረታ
ጠላትን በብቃት ድባቅ የሚመታ
የመብት ተሟጓች የሃገር መከታ
የሐቅ ጠበቃ የወገን አለኝታ።
ምሰሶው የፀና ችካል መሰረቱ
ፈተናን ያለፈ በየተግዳሮቱ
የጠላትን ህልሞች ያስቀረ በከንቱ
ማዕበል አውሎነፋስ መብረቅ የፈተነው
ከሴረኞች መድረክ የተሸጋገረው
ፍቱን ወርቅነቱን እያረጋገጠ
የጠላትን አንጎል ነርቩን ያናወጠ
ህዝባዊ ድጋፉን ከጎኑ አሰልፎ
በስኬት ላይ ስኬት ድልን ተጎናፅፎ



የትግል ድልድዩን እያጠነከረ
የሰላም መልዕክቱን ብርሃን ያበሰረ
ወደ ስኬት ገስጋሽ በንፁር አላማ
የሰላም ተምሳሌት የነፃነት አርማ
የማያወላውል አቋመ ጠንካራ
የእልፍ ዘመናት ትውልድ የታሪክ አሻራ
በክስተት ያለፈ ህዝባዊ ፍቱን ኃይል

አደራ ጠባቂ የጀግና ፅኑ ቃል።

መፍትሔ ለመስጠት ለጭቁን ሱባኤ
ለህዝባዊ ስልጣን የትግል መንስኤ
ለአገር መሰረት ነው ህዝባዊ ጉባኤ
የሁሉም ተሳትፎ የዜግነት ሚና
የዘመናት ስሪት የታሪክ ናሙና
የአንድነት ጉዞ ነው የስኬት ጎዳና።

*ከታጋይ ወርቅነህ መኮንን (ወርቄ)*